የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፸፮
አዲስ አበባ ነሐሴ ፩ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

25th Year No.76
ADDIS ABABA 7th August.2019

ማውጫ	Content
አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፵፯/፪ሺ፲፩ ዓ.ም	Proclamation No. 1147/2019
በተንቀሳቃሽ ንብረት ላይ የሚመሰረት የዋስትና መብት አዋጅ ..... ገጽ ፲፩፯፰፫	Movable Property Security Right Proclamation ..... Page 11380

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፵፯/፪ሺ፲፩

በተንቀሳቃሽ ንብረት ላይ የሚመሰረት የዋስትና መብት አዋጅ

ዋስትናው የተጠበቀ ዘመናዊ የብድር ሥርዓት እንዲኖር እና ግለሰቦችና ተቋማት ተንቀሳቃሽ ንብረታቸውን በማስያዝ ሥራ ላይ የሚውል አዲስ ካፒታል ማግኘት እንዲችሉ፣ በሂደትም በየደረጃው ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት፣ ተጨማሪ የሥራ ዕድሎችን ለመፍጠር፣ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ፣ የፋይናንስ ተደራሽነትንና ተጠቃሚነትን ለማስፋፋት፣ በዋናነት በኩተሞች ላይ ብቻ ውስን ሆኖ የቆየውን የባንክ አገልግሎትና ተደራሽነት ወደ ገጠሩ ማህበረሰብ ለማስፋፋትና ለማሳደግ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር የሚያስችል በመሆኑ፣

ተንቀሳቃሽ ንብረትን በዋስትና አስይዞ ብድር ማግኘት የሚቻልበትን ሥርዓት መዘርጋትና የማስፈጸሚያ መንገዱንም ቀልጣፋና ውጤታማ ማድረግ ተገቢ በመሆኑ፣

ለዋስትና በተያዘ ተንቀሳቃሽ ንብረት ላይ በተወዳዳሪ ባለመብቶች የሚነሳ የቀዳሚነት መብትን ለመወሰን የሚያስችል አንድ ወጥና ሁሉን አቀፍ የኤሌክትሮኒክ ምዝገባ ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩)መሠረት የሚከተለው ታውጇል፦

PROCLAMATION No. 1147/2019

A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR MOVABLE PROPERTY SECURITY RIGHT

WHEREAS, modern secured transactions system enables individuals and entities to use their movable assets as security for credit generating new productive capital, expands investments, creates more job opportunity, increases production and productivity, fosters access to and usage of financial products and services, creates opportunity to expand banking services to rural areas;

WHEREAS, it is necessary to provide for the creation of security right in movable property, ensure their publicity and effectiveness through efficient enforcement mechanisms;

WHEREAS, establishing single comprehensive electronic registration regime for secured transactions in movable property to determine priority right among competing claimants is necessary;

NOW, THEREFOR, in accordance with Article 55(1) of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Constitution, it is hereby **proclaimed as** follows:

ያንዱ ዋጋ Unit Price 52.70

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹፻፩ Negarit G P.O.Box 80001

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "በተንቀሳቃሽ ንብረት ላይ የሚመሰረት የዋስትና መብት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፵፯/፪ሺ፲፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

፩/ "የማይንቀሳቀስ ንብረት ተጓዳኝ" ማለት ከማይንቀሳቀስ ንብረት ጋር የተያያዘ ቢሆንም እንደተንቀሳቃሽ ንብረት የሚቆጠር ሀብት ነው፤

፪/ "ዋተገኘ የዋስትና መብት" ማለት በማህዝ ሀብት ወይም አዕምሯዊ ንብረት ላይ ያልተከፈለ ቀሪ ዋጋን ለማስፈጸም ወይም መያዣ ሰጪው በንብረቱ ላይ የባለቤትነት መብት እንዲያገኝ ለማድረግ የተፈፀመ ብድርን ለማስከፈል እንዲቻል በዚያው መጠን በንብረቱ ላይ የተገኘ የዋስትና መብት ነው፤

፫/ "የንግድ ተቋም" ማለት በንግድ ሕግ የተመለከተው የንግድ መደብር ነው፤

፬/ "በሰነድ የተደገፈ ሴኩሪቲ" ማለት ሰነዱን በያዘው ሰው ስም ወይም ለአምጪው ተብሎ የታዘዘ ሼር ወይም ቦንድ የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ ነው፤

፭/"የመያዣ መዝገብ" ማለት በተንቀሳቃሽ ንብረት ላይ በሸምጋኑት ወይም ከሀግ ወይም ከፍርድ የመነጨ የዋስትና መብት መረጃን መቀበያ፣ ማስቀመጫ እና ለሕዝብ ተደራሽ ማድረጊያ የኤሌክትሮኒክ ሥርዓት ነው፤

፮/ "የመያዣ ምዝገባ ጽሕፈት ቤት" ማለት የመያዣ ምዝገባ ሥርዓትን ለማስተዳደር የሚቋቋም ጽህፈት ቤት ነው፤

PART ONE

GENERAL PROVISIONS

1. Short Title

This Proclamation may be cited as "Movable Property Security Right Proclamation No. 1147/2019.

2. Definitions

In this Proclamation, unless the context otherwise requires:

1/ "**accessory to immovable**" means a corporeal asset that despite the fact that it is physically affixed to an immovable is treated as movable property;

2/ "**acquisition security right**" means a security right in a corporeal asset or intellectual property, which secures the obligation to pay any unpaid portion of the purchase price of the asset or other credit extended to enable the grantor to acquire right in the asset to the extent the credit is used for that purpose;

3/ "**business**" means a business specified under the Commercial Code of Ethiopia;

4/ "**certificated security**" means a document evidencing ownership of share or bond registered in the name of the holder or issued to a bearer;

5/ "**Collateral Registry**" means an electronic system for receiving, storing and making accessible to the public information about security right and non-consensual right in movable property;

6/ "**Collateral Registry Office**" means an office established to manage the Collateral Registry;

፯/ "ተወዳዳሪ ባለመብት" ማለት ገንዘብ ጠያቂ ወይም በዋስትና በተያዘ ንብረት ላይ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ጋር ተወዳዳሪ የመብት ጥያቄ ያለው ሌላ ሰው ነው፣

፰/ "የፍጆታ ዕቃዎች" ማለት መያዣ ሰጪው በዋናነት ለራሱ ወይም ለቤተሰቡ የቤት ውስጥ ፍጆታ የሚጠቀምባቸው ወይም ለመጠቀም ያዘጋጃቸው ዕቃዎች ናቸው፣

፱/ "የቁጥጥር ስምምነት" ማለት፦

ሀ) የኤሌክትሮኒክ ሴኩሪቲዎች ዋስትናን በተመለከተ በሰነድ አውጪው፣ በመያዣ ሰጪው እና ዋስትና ባለው ገንዘብ ጠያቂ መካከል የተደረገና አውጪው የመያዣ ሰጪው ተጨማሪ ፈቃድ ሳያስፈልገው ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ የሚሰጠውን ትዕዛዝ በቀጥታ የሚፈጽምበት የጽሑፍ ስምምነት ነው፣ ወይም

ለ) ከተቀማጭ ሂሳብ ላይ ክፍያ የማግኘት መብትን ለማስፈጸም በፋይናንስ ተቋሙ፣ በመያዣ ሰጪው እና ዋስትና ባለው ገንዘብ ጠያቂ መካከል የተደረገና የፋይናንስ ተቋሙ የመያዣ ሰጪው ተጨማሪ ፈቃድ ሳያስፈልገው በመያዣ ሰጪው ሂሳብ ውስጥ በተቀመጠ ገንዘብ ላይ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ የሚሰጠውን ትዕዛዝ በቀጥታ የሚፈጽምበት የጽሑፍ ስምምነት ነው፣

፲/ "ግዑዝ ሀብት" ማለት ገንዘብ፣ የሚተላለፍ የገንዘብ ሰነድ፣ የሚተላለፍ ሰነድ እና በሰነድ የተደገፉ ሴኩሪቲዎችን ጨምሮ ማንኛውም ዓይነት ዕቃ ነው፣

፲፩/ "ባለዕዳ" ማለት ዋስትና ለተገባለት ግዴታ ገንዘብ የመክፈል ወይም ግዴታውን የመፈጸም ኃላፊነት ያለበት ሰው ሲሆን ለዚሁ ዋስ የሆነንም ይጨምራል፣

7/ "competing claimant" means a creditor of a grantor or other person with right in the collateral that may be in competition with the right of a secured creditor in the same collateral;

8/ "consumer goods" means goods primarily used or intended to be used by the grantor for personal, family or household consumption;

9/ "control agreement" means:

a) with respect to electronic securities means an agreement in writing among the issuer, the grantor and the secured creditor, according to which the issuer agrees to follow instruction from the secured creditor with respect to the securities without further consent from the grantor; or

b) with respect to right to payment of funds credited to a deposit account means an agreement in writing among the financial institution, the grantor and the secured creditor, according to which the financial institution agrees to follow instruction from the secured creditor with respect to the payment of funds credited to the deposit account without further consent from the grantor;

10/ "corporeal asset" means any type of goods including money, negotiable instrument, negotiable documents and certificated securities;

11/ "debtor" means a person that owes payment or other performance of a secured obligation, whether or not that person is the grantor of the security right securing payment or other performance of that obligation, including a guarantor of a secured obligation;

፲፪/ "የተሰብሳቢ ሂሳብ ባለዕዳ" ማለት የተሰብሳቢ ሂሳብን የመክፈል ግዴታ ያለበት ሰው ሲሆን፣ ለሂሳቡ ክፍያ ዋስ የሆነን ወይም በሁለተኛ ደረጃ ዋስ የሆነ ሌላ ሰውን ይጨምራል፣

፲፫/ "ተቀማጭ ሂሳብ" ማለት ከሕዝብ ተቀማጭ ገንዘብ ለመሰብሰብ ፈቃድ በተሰጠው የፋይናንስ ተቋም ውስጥ ያለ ሂሳብ ነው፣

፲፬/ "መሣሪያ" ማለት ከንግድና ከሩጅታ ዕቃዎች ውጭ የሆነና መያዣ ሰጪው በዋናነት ለሥራው የሚጠቀምበት ወይም ሊጠቀምበት የያዘው ግዑዝነት ያለው ሀብት ነው፣

፲፭/ "ኤሌክትሮኒክ ሴኩሪቲዎች" ማለት ኤሌክትሮኒካዊ በሆነ መንገድ የተመዘገቡ፣ የሚተላለፉ እና በሰነድ ያልተደገፉ አክሲዮኖችና ቦንዶች ናቸው፣

፲፮/ "የግብርና ምርቶች" ማለት የበቀሉ ወይም በመብቀል ላይ ያሉ ወይም ወደፊት የሚበቅሉ ሰብሎች፣ ደንና የደን ውጤቶች፣ የቤት እንስሳት የሚወለዱትን ጨምሮ፣ የንብና የዶሮ ዕርባታ፣ ለግብርና ሥራ ጥቅም ላይ የሚውሉ ግብአቶች ወይም በግብርና ሥራ የተመረቱ፣ ወይም በምርት ሂደት ያልተቀየሩ የሰብል ወይም የእንስሳት ምርቶችንና ሌሎች የግብርና ውጤቶችን ያጠቃልላል፣

፲፯/ "የፋይናንስ ኪራይ" ማለት አከራዩ አንድ የተወሰነ የካፒታል ዕቃን ለተከራዩ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ተከፍሎ የሚያልቅ በሁለቱ ወገኖች ስምምነት የተወሰነ ክፍያ በየተወሰነ ጊዜ በመፈጸም እንዲጠቀምበት የሚያከራይበት፣ የኪራይ ስምምነቱ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ አከራዩ በካፒታል ዕቃው ላይ ሙሉ የባለቤትነት መብት ይዞ የሚቆይበትና የኪራይ ዘመኑ ሲያበቃ ሁለቱም ወገኖች ኮተስማሙ ተከራዩ የካፒታል ዕቃውን ሊገዛ የሚችልበት የኪራይ ዓይነት ነው፣

12/ **"debtor of the receivable"** means a person that owes payment of a receivable, including a guarantor or other person secondarily liable for payment of the receivable;

13/ **"deposit account"** means an account maintained by a financial institution authorized to receive deposit from the public;

14/ **"equipment"** means a corporeal asset other than inventory or consumer goods that is primarily used or intended to be used by the grantor in the operation of its business;

15/ **"electronic securities"** means shares and bonds registered and transferable electronically but not represented by a certificate;

16/ **"farm products"** include but not limited to crops grown, growing or to be grown; forest, timber and other wood products; livestock, born or unborn, bees and poultry and the produce and progeny thereof; supplies used or produced in a farming operation; or products of crops or livestock in their unmanufactured states.

17/ **"financial lease"** means a type of leasing by which a lessor provides a lessee against payment of mutually agreed installments over a specified period with the use of specified capital goods under which the lessor shall retain full ownership right on the capital goods during the period of the lease agreement, and, subject to agreement between the two parties, the lessee may have an option to purchase the capital good outright after the termination of the lease period at an agreed price.

፲፰/ "ታሳቢ ሀብት" ማለት ገና ያልተፈጠረ ወይም የዋስትና ስምምነቱ በሚፈጸምበት ጊዜ መያዣ ሰጪው ገና የባለቤትነት መብት ያላገኘበት ተንቀሳቃሽ ንብረት ነው፤

18/ "future asset" means a movable property, which does not exist or which the grantor does not have right in or the power to encumber at the time the security agreement is concluded;

፲፱/ "ታሳቢ ብድር" ማለት ዋስትና ያለው ግንዘብ ጠያቂ ከተበዳሪው ጋር ቀደም ሲል በመሰረተው የብድር ስምምነት መሠረት ለተበዳሪው ወደፊት የሚሰጠው ተጨማሪ ብድር ነው፤

19/ "future advance" means an additional credit where the secured creditor provides in the future to the debtor under the existing credit agreement;

፳/ "መያዣ ሰጪ" ማለት ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ግዴታ ማስፈፀሚያ ዋስትና ያስያዘ፣ በዋስትና ግዴታ የተያዘ ንብረትን ከነግዴታው የገዛ፣ የተላለፈለት፣ የተከራየ ወይም የመጠቀም ፈቃድ ያለው፣ በዱቤ ግዢ መሠረት የተከራየ ሰው ነው፤

20/ "grantor" means a person that creates a security right to secure either its own obligation or that of another person; a buyer or other transferee, lessee, or licensee of the collateral that acquires its right subject to a security right;

፳፩/ "የዱቤ ግዢ" ማለት አከራይና ተከራይ ባደረጉት ስምምነት መሠረት አከራይ በተወሰነ ጊዜ የሚደረግ ክፍያ እየተከፈለው አንድ የተወሰነ የካፒታል ዕቃን ተከራዩ እንዲጠቀምበት የሚፈቅድበት፣ እያንዳንዱ ክፍያ በተደረገ ቁጥር ለክፍያው ተመጣጣኝ በሆነ መቶኛ ልክ ለተከራይ የባለቤትነት መብት የሚተላለፍበትና ተከራይ የመጨረሻው ክፍያ እንዲፈጸመም በካፒታል ዕቃው ላይ ሙሉ የባለቤትነት መብት ወዲያውኑ የሚያገኝበት የኪራይ ዓይነት ነው፤

21/ "hire-purchase" means a type of leasing by which a lessor provides a lessee with the use of a specified capital goods, against payment of mutually agreed instalments over a specified period under which, with each lease payment, an equal percentage of the ownership is transferred to the lessee and, upon effecting of the last payment, the ownership of the capital goods shall automatically be transferred to the lessee;

፳፪/ "ግዑዝነት የሌለው ሀብት" ማለት ተሰብሳቢ ሂሳብን፣ ተቀማጭ ሂሳብን፣ የአእምሯዊ ንብረት መብትንና ከግዑዝ ንብረት ውጭ ያሉ ተመሳሳይ ተንቀሳቃሽ ንብረቶችን ያካትታል፤

22/ "incorporeal asset" means all types of movable property other than corporeal assets that shall include receivables, deposit accounts, intellectual property right;

፳፫/ "አዕምሯዊ ንብረት" ማለት በአገሪቱ አእምሯዊ ንብረት ህጎች የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፡፡

23/ "intellectual property" means will have a meaning that is given to it in the intellectual property law;

፳፬/ "የንግድ ዕቃ" ማለት ጥሬ እና በከፊል የተቀነባበሩትን ጨምሮ መያዣ ሰጪው በመደበኛ የንግድ ሥራ ሒደት ለሽያጭ ወይም ለኪራይ የያዘው ግዑዝ ሀብት ነው፤

24/ "inventory" means corporeal assets held by the grantor for sale or lease in the ordinary course of the grantor's business, including raw and semi-processed materials;

፳፭/ "ውህድ ወይም ምርት" ማለት አንድን ምርት ከሌላ ምርት ጋር በማዋሀድ ወይም በመቀላቀል የሚፈጠር አዲስ ይዘት ያለው ምርት ወይም ውህድ ነው፣

፳፮/ "ገንዘብ" ማለት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚታተሙ ሕጋዊ መገበያያ የገንዘብ ኖቶች እና የሚቀረጹ ሳንቲሞች፣ ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚፈጸም ክፍያ ተቀባይነት ያላቸውና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተገለጹ የሌላ ሀገር ሕጋዊ የመገበያያ የገንዘብ ኖቶች እና ሳንቲሞች ናቸው፣

፳፯/ "ተንቀሳቃሽ ንብረት" ማለት የንግድ ዕቃዎችን፣ የግብርና ምርቶችን፣ ግዑዝነት የሌላቸው ሀብቶችን፣ ግዑዝ ሀብቶችን፣ በሕግ ከልተከለከለ በስተቀር በመሬት ላይ የመጠቀም መብትን፣ በዱቤ ግዢ የሚገኝ መብት፣ በአደራ የተቀመጠ ንብረት ሠነድ፣ የአደራ መያዣ ደረሰኝ፣ የሽቀጦች ሞኒት፣ ንግድን ለዋስትና ማስያዝ፣ ባለቤትነትን በማስጠበቅ የሚደረግ ሽያጭ፣ የተሸጠ ንብረትን መልሶ ለመግዛት መብት የሚሰጥ ሽያጭ፣ በምስክር ወረቀት የሚረጋገጡ ሴኩሪቲዎች ላይ የሚመሠረት የዋስትና መብት፣ እና በመጋዘን ደረሰኝ ላይ ያለ የዋስትና መብትን፣ የሞተር ተሽከርካሪን፣ ተሳቢን፣ የእርሻ መሣሪያን፣ የኮንስትራክሽን መሣሪያን፣ የኢንዱስትሪ መሣሪያን ጨምሮ ሌሎች ከመሬት፣ ከቤት ወይም ከሕንጻ ውጭ ያሉ ንብረቶችን ያካትታል፣

፳፰/ "የሚተላለፍ ሰነድ" ማለት በሰነዱ ላይ የተገለጸውን ንብረት የመረከብ መብት የሚሰጥና ሊተላለፍ የሚችል እንደ ማጓጓዣ ሰነድ፣ ዋጭቸር ወይም በመጋዘን የተቀመጠ ዕቃ መቀበያ ደረሰኝ ነው፣

፳፱/ "የሚተላለፍ የገንዘብ ሰነድ" ማለት የሐዋላ ወረቀት፣ የተስፋ ሰነድ እና ከቼክ በስተቀር ሌላ ለአምጪው ወይም በስሙ ወይም ለታዘዘለት ተብሎ የተዘጋጀ ሰነድን ያካትታል፣

25/ **"mass or product"** means corporeal assets that are so physically associated or united with other corporeal assets that they have lost their separate identity;

26/ **"money"** means bank notes and coins which are legal tender issued and minted by the National Bank of Ethiopia; and notes and coins which are legal tender in any country outside Ethiopia as to which the National Bank of Ethiopia has declared to be acceptable for payment in Ethiopia;

27/ **"moveable property"** includes inventories, agricultural products, incorporeal assets, corporeal assets, the right to use land unless prohibited by pertinent laws; a security right under a hire-purchase agreement, security trust deed, trust receipt, commercial consignment, mortgage of a business, sale with ownership reserved, sale with right of redemption, security rights in certificated securities, and security rights in warehouse receipts, motor vehicle, trailer, agricultural machinery, construction machinery, industrial machinery, and other properties excluding land, house and building.;

28/ **"negotiable document"** includes a document, such as a bill of lading, way-bill, voucher or a warehouse receipt for goods warehoused that represents a right to delivery of corporeal assets and may be transferred by negotiation;

29/ **"negotiable instrument"** includes a bill of exchange, promissory note and other instruments except check issued to bearer, specified name or order;

ሰ/ "በህግ ወይም በፍርድ ግንዘብ ጠያቂ የሆነ" ማለት በዋስትና መያዣ ላይ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ወይም በሕግ ግንዘብ የመጠየቅ መብት ያገኘ ሰው ነው፡

ሰ፩/ "ማስታወቂያ" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት ዋስትና ባለው ግንዘብ ጠያቂ ወይም ፈቃድ በተሰጠው ሰው በመያዣ መመዝገቢያ ሥርዓት ውስጥ የሚካተት የመጀመሪያ ምዝገባ፣ የማስተካከያ ምዝገባ ወይም የስረዛ ምዝገባ ነው፡

ሰ፪/ "የእጭር ጊዜ መጠቀሚያ ኪራይ" ማለት በአከራዩ እጅ የሚገኝ አንድ የተወሰነ የካፒታል ዕቃን ተከራዩ በሁለቱ ወገኖች ስምምነት የተወሰነ ኪራይ በመክፈል ከሁለት ዓመት ላልበለጠ ጊዜ እንዲጠቀምበት የሚከራይበት የኪራይ ዓይነት ነው፡

ሰ፫/ "ቀደምት ሕግ" ማለት ይህ አዋጅ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በሥራ ላይ የነበረ ሕግ ነው፡

ሰ፬/ "ቀደምት የዋስትና መብት" ማለት ይህ አዋጅ ከመፅናቱ በፊት በተፈጸመ የዋስትና ስምምነት የተሸፈነ መብት ነው፡

ሰ፭/ "ይዞታ" ማለት አንድ ሰው ወይም ተወካዩ አንድን ግዑዝ ንብረት በራሱ ወይም በሌላ ሰው ኃላፊነት ሥር እንዲሆን ማድረግ ነው፡

ሰ፮/ "ተያያዥ ገቢ" ማለት ከዋስትና መያዣው የሚገኝ ማንኛውም ገቢ ሲሆን፣ በሽያጭ፣ በማስተላለፍ፣ በመሰብሰብ፣ በማከራየት ወይም በፈቃድ የተገኘ ወይም የፍሬ ገቢ፣ የመድን ገቢ፣ በዋስትና ከተያዘው ንብረት ብልሽት፣ ጉዳት ወይም መጥፋት ጋር ተያይዞ የሚሰበሰብ ገቢንና በዚሁ ገቢ አማካይነት የተገኘ ተጨማሪ ገቢን ያካትታል፡

30/ "non-consensual creditor" means a creditor that has obtained a right in the collateral, on the basis of a court order or applicable law;

31/ "notice" includes an initial notice, an amendment notice or a cancellation notice submitted to the Collateral Registry by the secured creditor or other authorized person under this Proclamation;

32/ "operating lease" means a type of leasing for a period of time not exceeding two years, by which a lessor provides a lessee against payment of mutually agreed rent with the use of specified capital goods that the lessor has at hand;

33/ "prior law" means the law in force before the entry into force of this Proclamation;

34/ "prior security right" means a right covered by a security agreement entered into before the entry into force of this Proclamation;

35/ "possession" means the actual possession of a corporeal asset by a person or its representative, or constructive possession by an independent person that acknowledges holding it for that person;

36/ "proceeds" means whatever is received in respect of the collateral, including what is received as a result of sale or other disposition or collection, lease or licence of the collateral, fruits, insurance proceeds, claims arising from defects in, damage to or loss of the collateral, and proceeds of proceeds;

፴፯/ "ተሰብሳቢ ሂሳብ" ማለት ተንቀሳቃሽ ንብረት ሲሆን ከሚተላለፍ የገንዘብ ሰነድ፣ ከተቀማጭ ሂሳብ እና ከዋስትና የሚገኝ የክፍያ መብትን ሳይጨምር ገንዘብ የመክፈል መብት ነው፣

37/ **"receivable"** means a right to payment of a monetary obligation, excluding a right to payment evidenced by a negotiable instrument, a right to payment of funds credited to a deposit account and a right to payment under security;

፴፰/ "የታወቀ ገበያ" ማለት ዋጋ በይፋ የሚገለጽበት እና/ወይም በንግድ አሰራር ተገቢ ነው ተብሎ የሚታመንበት የተለመደና የታወቀ ገበያ ማለት ነው፣

38/ **"recognized market"** means a market in which prices are stated publicly and/or presumed to be commercially reasonable;

፴፱/ "መዝጋቢ" ማለት ምዝገባው በሚጠይቀው መሥፈርት መሠረት መረጃዎችን በመያዣ መመዝገቢያ ሥርዓት ውስጥ የሚመዘግብ ወይም የሚያካትት ሰው ነው፣

39/ **"registrant"** means the person who submits the prescribed registry notice form to the Collateral Registry;

፵/ "ሬጅስትራር" ማለት የመያዣ ምዝገባ ሥርዓቱን እንዲያስተዳድር እና እንዲቆጣጠር በመንግሥት የሚሾም ሰው ነው፣

40/ **"Registrar"** means a person to be appointed by the government to supervise and administer the operations of the Collateral Registry;

፵፩/ "መረጃ" ማለት በመያዣ መመዝገቢያ ሥርዓት ውስጥ የተቀመጠ፣ የተጠበቀ፣ የተደራጀና ለሕዝብ ክፍት የሆነ የተመዘገበ መረጃ ነው፣

41/ **"records"** means the information in all registered notices stored by the Collateral Registry, consisting of the records that are publicly accessible and the records that have been archived;

፵፪/ "ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ" ማለት የዋስትና መብት ያለው ወይም በሀግ ወይም በፍርድ የገንዘብ ጠያቂነት መብት የተሰጠው ሰው ነው፣

42/ **"secured creditor"** means a person that has a security right or non-consensual creditor.

፵፫/ "የዋስትና ስምምነት" ማለት ተዋዋይ ወገኖች የዋስትና ስምምነት ብለው ባይሰይሙትም በመያዣ ሰጪውና በመያዣተቀባዩ መካከል የተፈረመ የዋስትና መብት የሚፈጥር ስምምነት ነው፣

43/ **"security agreement"** means an agreement, regardless of whether the parties have denominated it as a security agreement, between a grantor and a secured creditor that provides for the creation of a security right;

፵፬/ "የዋስትና መብት" ማለት ተዋዋይ ወገኖች የዋስትና መብት ብለው ባይሰይሙትም በንብረቱ ዓይነት፣ በመያዣ ሰጪውና ተቀባዩ እና ዋስትና በተገባለት ግዴታ ላይ ሳይወሰን የክፍያ ወይም ሌላ ግዴታን ለማስፈጸም በተንቀሳቃሽ ንብረት ላይ የሚፈጠር መብት ነው፣

44/ **"security right"** means a property right in movable property that is created by an agreement to secure payment or other performance of an obligation, regardless of whether the parties have denominated it as a security right, and regardless of the type of property, the status of the grantor or secured creditor, or the nature of the secured obligation;

፵፭/ "መለያ ቁጥር" ማለት በሻሲ ወይም በሌላ የፋብሪካ ምርት አካል ላይ የሚገኝ መለያ ቁጥር ነው፣

፵፮/ "መለያ ቁጥር ያለው መያዣ" ማለት በአምራቹ በቋሚነት የተጻፈ ወይም የተለጠፈ መለያ ቁጥር ያለው ሞተር ተሽከርካሪ፣ ተሳቢ፣ የእርሻ መሣሪያ፣ የኮንስትራክሽን መሣሪያ፣ የኢንዱስትሪ መሣሪያ እና ሌላ መለያ ቁጥር ያለው ዕቃ ነው፣

፵፯/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፣

፵፰/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለፀው የሴትንም ጾታ ያካትታል።

፫. የተፈፃሚነት ወሰን

፩/ ይህ አዋጅ ለብድር ክፍያ ወይም ለሌላ ግዴታ አፈጻጸም በስምምነት በሚመሠረቱ በተንቀሳቃሽ ንብረት መብቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

፪/ ይህ አዋጅ፦

ሀ) በገበያ በሚሸጡ ሴኩሪቲዎች ላይ የሚመሠረት የዋስትና መብት ላይ፣

ለ) የባሕር ሕግ ተፈፃሚ የሆነበት መርከብና ለአገልግሎቱ በሚውሉ ተጓዳኞች ላይ የሚመሰረት የዋስትና መብት ላይ፣

ሐ) በኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን በተመዘገበ አውሮፕላን ላይ የሚገኝ የተጠቃሚነት መብት ላይ፣

መ) በዚህ አዋጅ ካልተገለፀ በስተቀር ብድር እስኪመለስ ድረስ ገንዘብ ጠያቂው በሕግ እንዲይዘው በተፈቀደ ንብረት ላይ፣ እና

ሠ) አንድ ተያያዥ ገቢ ከዚህ አዋጅ የተፈፃሚነት ወሰን ውጭ ከሆነ፣ በገቢው ላይ ሌሎች ሕጎች ተፈጻሚነት ካላቸውና የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችን የሚሸፍኑና የሚፈቅዱ ከሆነ፣ ይህ አዋጅ በተያያዥ ገቢው የዋስትና መብት ላይ፣

ተፈፃሚ አይሆንም።

45/ **"serial number"** means the serial number located on the chassis or body frame;

46/ **"serial-numbered collateral"** means a motor vehicle, trailer, agricultural machinery, construction machinery or industrial machinery and others that have a serial number permanently marked on or attached by the manufacturer;

47/ **"person"** means natural or legal person.

48/ a expression in the masculine gender includes the feminine.

3. Scope of Application

1/ This Proclamation shall apply to rights in movable property created by agreement that secure payment of credit or other performance of an obligation.

2/ This Proclamation shall not apply to:

a) security right in securities traded on exchanges;

b) a mortgage of a ship with all accessories required for its use subject to the Maritime Code;

c) an interest in an aircraft subject to the registration by the Ethiopian Civil Aviation Authority; and

d) except as otherwise provided in this Proclamation, a lien or other interest given by law; and

e) security right in proceeds of collateral if the proceeds are a type of asset that is outside the scope of this Proclamation to the extent that other laws applies to security right in those types of asset and governs the matters addressed in this Proclamation.

ሸ/ ይህ አዋጅ በማይንቀሳቀሱ ንብረቶች ሕግ መሠረት በማይንቀሳቀስ ንብረት ተጓዳኝ ላይ የሚፈጠር ዋስትናን አይከለክልም።

ክፍል ሁለት

የዋስትና መብት አመሠራረት

፬. የዋስትና መብት በስምምነት የሚመሠረት ስለመሆኑና ይዘቱ

፩/ የዋስትና መብት የሚመሠረተው በስምምነት ሆኖ መያዣ ሰጪው ለዋስትና ባቀረበው ንብረት ላይ የባለቤትነት ወይም የማስያዝ መብት ሊኖረው ይገባል።

፪/ በዱቤ ግዥ ውል መሠረት በተገኘ የካፒታል ዕቃ ላይ ተከራይ የዋስትና መብት መፍጠር ይችላል። ሆኖም የመብቱ ከፍተኛ መጠን ከዕቃው ዋጋ ላይ ለአከራይ ሊከፈል የሚገባው ቀሪ ዕዳ ተቀንሶ በሚቀረው መጠን ላይ ብቻ የተወሰነ ይሆናል።

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቢኖርም የዋስትና መብት ስምምነት በታሳቢ ሀብት ላይ መመስረት ይቻላል።

፬/ የዋስትና መብት ተንቀሳቃሽ ወይም የማይንቀሳቀስ ንብረት ተጓዳኝን በመያዣነት ሊይዝ ይችላል። ሆኖም ተጓዳኙ ከተንቀሳቃሽ ወይም ከማይንቀሳቀስው ንብረት ጋር በአካል መያያዙ መብቱን ቀሪ አያደርግም።

፭/ የዋስትና ስምምነት በጽሑፍ የተደገፈና በመያዣ ሰጪው ፊርማ የተረጋገጠ ሆኖ፦

ሀ) የመያዣ ሰጪውንና የዋስትና ተቀባዩን ማንነት፣

ለ) ዋስትና የተገባለትን ግዴታ፣ እና

ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ መሠረት መያዣውን፣

መግለጽ ይኖርበታል።

3/ This Proclamation shall not prevent creation of an encumbrance in accessories to immovable under immovable property law.

PART TWO

CREATION OF A SECURITY RIGHT

4. Creation of a Security Right by Agreement and its Elements

1/ A security right shall be created by a security agreement, provided that the grantor has right in the asset to be encumbered or the power to encumber it.

2/ A lessee under a hire-purchase may create a security right in capital goods but the maximum amount realizable under the security right is limited to the goods value in excess of the amount owed to the lessor.

3/ Notwithstanding to Sub-article (1) of this Article, security agreement may provide for the creation of a security right in a future asset,

4/ A security right may encumber and continue in an accessory to movable or immovable, and a security right is not extinguished by an affixation of the accessory to movable or immovable property.

5/ A security agreement shall be evidenced by a writing that is signed by the grantor, and:

a) identify the secured creditor and the grantor;

b) describe the secured obligation; and

c) describe the collateral as provided in Article 6.

፭. ዋስትናቸው ሊጠበቅ የሚችል ግዴታዎች

አንድ የዋስትና መብት የታወቀ ወይም ታሳቢ የሆነ፣ የተረጋገጠ ወይም ሊረጋገጥ የሚችል፣ በቅድመ ሁኔታ ወይም ያለ ቅድመ ሁኔታ፣ የተቆረጠ ወይም ተለዋዋጭ የሆነ አንድ ወይም ከአንድ በላይ ግዴታዎችን ሊሸፍን ይችላል።

፮. የመያዣው እና የዋስትናው ግዴታ መግለጫ

፩/ መያዣው እና የዋስትናው ግዴታ በዋስትና ስምምነቱ ውስጥ በበቂ ሁኔታና በግልጽ ሊለዩ በሚያስችል መልኩ ሊገለጹ ይገባል።

፪/ መግለጫው የዋስትና መያዣውን በዝርዝር፣ በምድብ፣ በዓይነት፣ ወይም በብዛት በመለየት ማስቀመጥ አለበት።

፫/ ዋስትናው የተጠበቀ ግዴታ አሁን የተገባ ወይም ወደፊት የሚገባ ተብሎ፣ በአንድ ጠቅላላ ምድብ ወይም እያንዳንዱ ተለይቶ እና ዋስትና የተገባለትን ግዴታ ከፍተኛ መጠን በማመልከት መገለጽ ይኖርበታል።

፯. በተያያዥ ገቢ ላይ ስለሚኖር መብት

፩/ በአንድ ሀብት ላይ ያለ የዋስትና መብት በሀብቱ ላይ ተለይተው ሊታወቁ የሚችሉ ተያያዥ ገቢዎችን ያካትታል።

፪/ ተያያዥ ገቢ በተቀማጭ ሂሳብ ውስጥ ገቢ ከተደረገ ወይም ከሌላ ገንዘብ ጋር ከተቀላቀለ:-

ሀ) የተቀላቀለው ገንዘብ ተለይቶ መታወቂ ቢያከትምም የዋስትና መብቱ የተቀላቀለውን ተያያዥ ገቢ ይከተላል፣

ለ) በውሀድ ንብረት ላይ ያለ የዋስትና መብት ንብረቶቹ ከመዋሀዳቸው በፊት በነበረው ተያያዥ ገቢ መጠን ላይ ይገደባል፣

5. Obligations That may be Secured

A security right may secure one or more obligations of any type, present or future, determined or determinable, conditional or unconditional, fixed or fluctuating.

6. Description of Collateral and Secured Obligation

1/ The collateral and secured obligation shall be described in the security agreement in a manner that reasonably allows their identification.

2/ A description shall reasonably identify the collateral by specific listing, category, a type of collateral, or quantity.

3/The secured obligation may be described as all obligation currently owed and to be incurred in the future, generically or specifically, including by a reference to the maximum amount secured by the security right.

7. Right to Proceeds

1/ A security right in an asset shall extend to its identifiable proceeds.

2/ Where proceeds in the form of funds credited to a deposit account or money are commingled with other assets of the same kind:

a) the security right extends to the commingled assets, notwithstanding that the proceeds have ceased to be identifiable;

b) the security right in the commingled assets is limited to the amount of the proceeds immediately before they were commingled; and

ሐ) ከውሀደት በኋላ በማንኛውም ጊዜ የተዋሀደው ገንዘብ ከውህደቱ በፊት ከተቀላቀለው ቅያሬ ዝቅ ያነስ ከሆነ፣ በተዋህደው ገንዘብ ላይ ያለ የዋስትና መብት ጥያቄው በቀረበበት ወቅት በሚኖረው መጠን ላይ የተገደበ ይሆናል።

፰. ውህድ ወይም ምርት ውስጥ የተቀላቀሉ ግዑዝ ሃብቶች

ግዑዝ ሀብት ከሌላ ተመሳሳይ ሀብት ወይም ምርት ጋር ቢዋሀድ እንኳን በሃብቱ ላይ የተመሠረተው የዋስትና መብት ወደ ውህድ ወይም ምርቱ ይተላለፋል።

፱. የዋስትና መብት እንዳይመሠረት የሚገድቡ ስምምነቶች

፩/ በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የዋስትና መብት መመሥረትን የሚገድብ ስምምነት በባለመብቱና በባለዕዳው መካከል ቢኖርም ከዚህ በተቃራኒ በመያዣ ሰጪውና ዋስትና ባለው ገንዘብ ጠያቂ መካከል የተፈጠረ የዋስትና መብት ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቢኖርም መያዣ ሰጪው በንዑስ አንቀጹ የተመለከተውን ውል በመጣሱ ምክንያት ካለበት ግዴታና ኃላፊነት ነጻ ሊሆን አይችልም። ሆኖም ሌላኛው ተዋዋይ ወገን፦

ሀ) ለተሰብሳቢ ሂሳቡ ወይም ለዋስትና ስምምነቱ መነሻ የሆነው ውል ተጥሷል በሚል ምክንያት ብቻ ውሉን መተው፣ ወይም

ለ) በውሉ አለመከበር ምክንያት በመያዣ ሰጪው ላይ ሊኖረው የሚችለውን ማንኛውንም መብት ዋስትና ካለው ገንዘብ ጠያቂ ላይ ማንሳት፣

አይችልም።

c) if at any time after the commingling, the amount of the commingled funds or money is less than the amount of the proceeds immediately before they were commingled, the security right in the commingled funds or money is limited to the available balance at the time of the claim.

8. Corporeal Assets Commingled in a Mass or Product

A security right in a corporeal asset that is commingled in a mass of assets of the same kind or product extends to the mass or product.

9. Contractual Limitations on the Creation of a Security Right

1/ A security right in a receivable is effective as between the grantor and the secured creditor and as against the debtor of the receivable despite an agreement limiting the grantor's right to create a security right entered into between the grantor and the debtor of the receivable or any subsequent secured creditor;

2/ Nothing in Sub Article (1) of this Article affects any obligation or liability of the grantor for breach of the agreement referred to in that Article, but the other party to the agreement may not:

a) avoid the contract giving rise to the receivable or the security agreement on the sole ground of the breach of that agreement;or

b) raise against the secured creditor any claim the party may have against the grantor as a result of that breach.

ቸ/ ይህ አንቀጽ ተፈፃሚ የሚሆነው፡-

ሀ) ከፋይናንስ አገልግሎት በስተቀር ከዕቃ ወይም ከአገልግሎት አቅርቦት ወይም ከኪራይ ውል፣

ለ) ከግንባታ ውል ወይም ከማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ወይም ከኪራይ ውል፣ እና

ሐ) ከአዕምሯዊ ንብረት ሽያጭ፣ ኪራይ ወይም የመጠቀም ፈቃድ ውል፣

በሚመነጩ ተሰብሳቢ ሂሳቦች ላይ ብቻ ነው፡፡

፬/ መያዣ ሰጪው በተቀማጭ ሂሣብ ላይ የዋስትና መብት የመፍጠር መብቱን በማንኛውም ሁኔታ የሚገድብ ውል ከፋይናንስ ድርጅት ጋር ቢዋዋልም እንኳን በተቀማጭ ሂሳቡ ውስጥ ገቢ ከተደረገ ግንዘብ ላይ ክፍያ የማግኘት የዋስትና መብት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

፲. ክፍያን ወይም ሌላ ግዴታን ለማስፈጸም ዋስትና ወይም ደጋፊ ስለሚሆኑ ግላዊ ወይም የንብረት መብቶች

፩/ ግዑዝነት በሌለው ሀብት ወይም በተላላፊ የግንዘብ ሰነዶች ላይ ዋስትና ያለው ግንዘብ ጠያቂ ዋስትናውን በአዲስ ስምምነት ማስተላለፍ፣ ሳያስፈልግ ለክፍያ ወይም ለሌላ ግዴታ አፈጻጸም መጠቀም ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተገለጸው መብት ሲተላለፍ፣ የሚችለው በሌላ አዲስ ስምምነት ከሆነ መያዣ ሰጪው ይህን የተጠቃሚነት መብት ዋስትና ላለው ግንዘብ ጠያቂ የማስተላለፍ ግዴታ ይኖርበታል፡፡

፲፩. በተላላፊ ሰነዶች የተሸፈኑ ግዑዝ ሀብቶች

በተላላፊ ሰነድ ላይ የተመሠረተ የዋስትና መብት በሰነዱ በተካተተ ግዑዝ ሀብት ላይም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

3/ This Article applies only to receivables arising from:

a) a contract for the supply or lease of goods or services other than financial services;

b) a construction contract or a contract for the sale or lease of immovable property; and

c) a contract for the sale, lease or licence of intellectual property.

4/ A security right in a right to payment of funds credited to a deposit account is effective notwithstanding an agreement between the grantor and the financial institution limiting in any way the grantor's right to create a security right.

10. Personal or Property Rights Securing or Supporting Payment or Other Performance

1/ A secured creditor with a security right in an incorporeal asset or a negotiable instrument has the benefit of any personal or property right that secures or supports payment or other performance of the collateral without a new act of transfer.

2/ If the right referred to in Sub Article (1) of this Article is transferable only with a new act of transfer, the grantor is obliged to transfer the benefit of that right to the secured creditor.

11. Corporeal Assets Covered by Negotiable Documents

A security right in a negotiable document extends to the corporeal asset covered by the document.

፲፪. ከአዕምሯዊ ንብረት መብት ጋር ስለተያያዙ ግዑዝ ሀብቶች

በአዕምሯዊ ንብረት መነሻነት በተፈጠረ ግዑዝ ሀብት ላይ የተመሠረተ የዋስትና መብት አዕምሯዊ ንብረቱን አያካትትም፣ በአዕምሯዊው ንብረት ላይ የተመሠረተ የዋስትና መብትም ግዑዝ ሀብቱን አይሸፍንም።

ክፍል ሦስት

የዋስትና መብት በሦስተኛ ወገን ላይ ስላለው ተፈፃሚነት

፲፫. የዋስትና መብት በሦስተኛ ወገን ላይ ተፈፃሚ የሚሆንባቸው መንገዶች

በተንቀሳቃሽ ንብረት ላይ የተመሠረተ የዋስትና መብት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው፦

ሀ/ የዋስትና መብቱን አስመልክቶ በዋስትና መዝገብ ውስጥ ማስታወቂያው ዋስትና ባለው ገንዘብ ጠያቂ ከተመዘገበ፣

ለ/ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ገንዘብ፣ ተላላፊ የገንዘብ ሰነዶች፣ ተላላፊ ሰነዶችና በሰነድ የተደገፉ ሴኩሪቲዎች በአንቀጽ ፶፮ መሠረት በይዞታው ሥር ካደረገ፣ ወይም

ሐ/ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ወደተቀማጭ ሂሳብ ገቢ የሚደረግ ገንዘብ ወይም በኤሌክትሮኒክ ሴኩሪቲዎች ዋስትና ላይ የቁጥጥር ስምምነት ካለው፣

ነው።

፲፬. የተያያዥ ገቢ፣ የውሁድ ወይም የምርት የዋስትና መብት በሦስተኛ ወገን ላይ ስለሚኖረው ተፈፃሚነት

ሀ/ በአንድ ንብረት ላይ የተመሠረተ የዋስትና መብት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ከሆነ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯ መሠረት በንብረቱ ተያያዥ ገቢ ላይም በመያዣ ሰጪውና በዋስትና ተቀባዩ መካከል ሌላ ተጨማሪ ስምምነት ሳያስፈልግ ተፈጻሚ ይሆናል። ይህ የሚሆነው ተያያዥ ገቢው ገንዘብ፣ ተሰብሳቢ ሂሣብ፣ የሚተላለፍ የገንዘብ ሰነድ ከሆነና ወደ ተቀማጭ ሂሣብ ገቢ ከተደረገ ገንዘብ ላይ ክፍያ የማግኘት መብት ካለ ነው።

12. Corporeal Assets with Respect to Which Intellectual Property is Used

A security right in a corporeal asset with respect to which intellectual property is used shall not extend to the intellectual property and a security right in the intellectual property shall not extend to the corporeal asset.

PART THREE

EFFECTIVENESS OF A SECURITY RIGHT AGAINST THIRD-PARTY

13. Methods of Effectiveness of Security Right Against Third-Party

A security right in movable property shall be effective against third parties if:

1/ a notice with respect to the security right is registered in the Collateral Registry by the secured creditor;

2/ the secured creditor has possession of the corporeal asset that is money, negotiable instruments, negotiable documents and certificated securities or subject to Article 56 or.

3/ the secured creditor has acquired control over the right to payment of funds credited to a deposit account or an electronic security.

14. Effectiveness of Security Right in Proceeds, Mass's and Product's Against Third-Party

1/ If a security right in an asset is effective against third parties, a security right in any proceeds of that asset arising under Article 7 is effective against third parties without any further act by the grantor or the secured creditor if the proceeds are in the form of money, receivables, negotiable instruments or rights to payment of funds credited to a deposit account.

፪/ በአንድ ሀብት ላይ የተመሠረተ የዋስትና መብት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተገለጹት ተያያዥ ገቢዎች በስተቀር በሌሎች ገቢዎች ላይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯ መሠረት የሚፈጠረው የዋስትና መብት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው:-

ሀ) ገቢዎቹ ከተፈሩ በኋላ ለአሥር የሥራ ቀናት፣ እና

ለ) በገቢዎቹ ላይ ያለ የዋስትና መብት አሥሩ የሥራ ቀናት ከማለቃቸው በፊት አግባብ በሆነው የዋስትና ዓይነት ላይ ተፈፃሚ ከማድረጊያ መንገዶች በአንዱ አማካኝነት የዋስትና መብቱ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ከሆነ፣

ነው።

፫/ በግዑዝ ሀብቶች ላይ የተመሠረተ የዋስትና መብት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ከሆነ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፰ መሠረት በውህድ ወይም በምርት ላይ ያለተጨማሪ ሁኔታ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

፲፭. <u>በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ የሆኑ የዋስትና መንገዶች ለውጥ</u>

የዋስትና መብት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ የሚሆንባቸው መንገዶች ቢለወጡም በለውጡ ሂደት የጊዜ ክፍተት እስከሌለ ድረስ ተፈፃሚነቱ ይቀጥላል።

፲፮. <u>የዋስትና መብትን ስለማስተላለፍ</u>

፩/ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ በዋስትናው ላይ ያለውን የዋስትና መብት በሙሉ ወይም በከፊል ካስተላለፈ ይህንኑ የሚገልጽ የማስተካከያ ማስታወቂያ ማስመዝገብ ይችላል።

፪/ የተላለፈ የዋስትና መብት የማስተካከያ ማስታወቂያ በመዝገብ ላይ ቢመዘገብም ባይመዘገብም ተፈጻሚ ይሆናል።

2/ If a security right in an asset is effective against third parties, a security right arising under Article 7 in any type of proceeds other than the types of proceeds referred to in Sub Article (1) of this Article is effective against third parties:

a) for ten working days after the proceeds arise; and

b) thereafter, only if the security right in the proceeds is made effective against third parties by one of the methods applicable to the relevant type of collateral before the expiry of ten working days.

3/ If a security right in a corporeal asset is effective against third parties, a security right in a mass or product to which the security right extends under Article 8 is effective against third parties without any further act.

15. <u>Changes in the Methods of Security Right for Achieving Third-Party Effectiveness</u>

A security right continues to be effective against third parties despite a change in the methods for achieving third-party effectiveness, provided that there is no time gap when the security right is not effective against third parties.

16. <u>Transfer of a Security Right</u>

1/ If the secured creditor transfers a security right or a part of it, it may register an amendment notice to reflect the transfer.

2/ A transfer of a security right is effective whether or not an amendment notice has been registered.

፲፯. ወደ ተቀማጭ ሂሳብ ገቢ ከሚደረግ ገንዘብ ላይ ክፍያ የመጠየቅ መብት

ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ፦

፩/ የፋይናንስ ተቋሙን ተጠቃሚ የሚያደርግ የዋስትና መብት በመመሥረት፣

፪/ የቁጥጥር ስምምነት በመፈረም፣ ወይም

፫/ የተቀማጭ ሂሳብን በይዞታ ሥር በማድረግ፣

ወደ ተቀማጭ ሂሳብ ገቢ ከሚደረግ ገንዘብ ላይ ክፍያ ለማግኘት የሚያስችል የቁጥጥር መብት ይኖረዋል።

17. Right to Payment of Funds Credited to a Deposit Account

The secured creditor acquires control over a right to payment of funds credited to a deposit account:

1/ upon the creation of the security right in favour of the financial institution;

2/ upon the conclusion of a control agreement; or

3/ when the secured creditor becomes the deposit account holder.

፲፰. ተላላፊ ሰነድና በሰነዱ የሚሸፈኑ ግዑዝ ሀብቶች

፩/ በተላላፊ ሰነድ ላይ ያለ የዋስትና መብት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ከሆነ መብቱ በሰነዱ በተሸፈነው ንብረት ላይም ተፈፃሚ ይሆናል።

፪/ የተላላፊ ሰነድ ዋስትና ባለው ገንዘብ ጠያቂ ይዞታ ሥር ከሆነ የዋስትና መብቱ በሰነዱ በተሸፈኑ ንብረቶችና በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈጻሚ እንዲሆን ያደርጋል።

18. Negotiable Document and Corporeal Assets Covered by that Document

1/ If a security right in a negotiable document is effective against third parties, the security right that extends to the corporeal asset covered by the document is also effective against third parties.

2/ During the period when a negotiable document covers a corporeal asset, a security right in the asset may also be made effective against third parties by the secured creditor's possession of the document.

፲፱. ኤሌክትሮኒክ ሴኩሪቲዎች

ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ኤሌክትሮኒክ ሴኩሪቲዎችን መቆጣጠር የሚችለው፦

፩/ የሴኩሪቲዎቹን ይዞታ ለመመዝገብ ሲባል በአውጪው ወይም በወኪሉ በተዘጋጀ መዝገብ ላይ የዋስትና መብቱን መግለጫ በመፃፍ ወይም ዋስትና ያለውን ገንዘብ ጠያቂ ስም በመመዝገብ፣ ወይም

፪/ የቁጥጥር ስምምነት በመፈፀም፣

ነው።

19. Electronic Securities

The secured creditor acquires control over an electronic security upon:

1) the notation of the security right or entry of the name of the secured creditor in the books maintained by or on behalf of the issuer for the purpose of recording the name of the holder of the securities; or

2) the conclusion of a control agreement.

ክፍል አራት

የመያዣ መዝገብ

፳. የመያዣ ምዝገባ ጽሕፈት ቤት መቋቋም

የተንቀሳቃሽ ንብረት ዋስትና ምዝገባ ጽሕፈት ቤት በደንብ ይቋቋማል።

፳፩. የመያዣ መዝገብ መቋቋም

የዋስትና መብትን እና በሀማ ወይም በፍርድ የገንዘብ ጠያቂነት መብት የተሰጠውን ሰማመለከት መረጃ ለመቀበል፣ ለማስቀመጥና ለሕዝብ ተደራሽ የማድረግ ዓላማ ያለው የተንቀሳቃሽ ንብረት የመያዣ መዝገብ ይቋቋማል።

፳፪. መያዣ ሰጪው ለዋስትና ምዝገባ የሚሰጠው ፈቃድ

ሀ/ በመያዣ መዝገብ ውስጥ የማሳወቂያ ምዝገባ የሚከናወነው ዋስትና ባለው ገንዘብ ጠያቂ ወይም በሀጋዊ ወኪሉ ነው።

ለ/ መያዣ ሰጪው በጽሑፍ ካልፈቀደ በስተቀር የመጀመሪያ የዋስትና መብት ማስታወቂያ ምዝገባ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

ሐ/ መያዣ ሰጪው በጽሑፍ ካልፈቀደ በስተቀር በዋስትና ስምምነት ያልተሸፈነ መያዣን ለመጨመር የሚደረግ የማስታወቂያ ማሻሻያ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

መ/ ተጨማሪ መያዣ ሰጪ የሚሆነው ሰው በጽሑፍ ካልፈቀደ በስተቀር መያዣ ሰጪ ለመጨመር የሚደረግ የማስታወቂያ ማሻሻያ ተፈፃሚነት የለውም።

ሠ/ በጽሑፍ የተደረገ የዋስትና ስምምነት መያዣ ሰጪው ማስታወቂያው እንዲመዘገብ እንደፈቀደ ይቆጠራል።

ረ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) መሠረት የዋስትና ስምምነት ከቀረበ የመያዣ መዝገቡ መያዣ ሰጪው ምዝገባ እንዲደረግ ፈቃድ ስለመስጠቱ ማረጋገጫ አይጠይቅም።

PART FOUR

COLLATERAL REGISTRY

20. Establishment of the Collateral Registry Office

The Collateral Registry Office shall be established by regulation.

21. Establishment of the Collateral Registry

The Collateral Registry shall be established for the purposes of receiving, storing and making information accessible to the public in registered notices with respect to security right and right of non-consensual creditors.

22. Grantor's Authorization for Registration Security Right

1/ Registration of notices in the collateral registry will be conducted by the secured creditor or an authorized representative.

2/ Registration of an initial notice is ineffective unless authorized by the grantor in writing.

3/ Registration of an amendment notice that adds collateral not covered in the security agreement is ineffective unless authorized by the grantor in writing.

4/ Registration of an amendment notice that adds a grantor is ineffective unless authorized by the additional grantor in writing.

5/ A written security agreement is sufficient to constitute authorization by the grantor for the registration of a notice.

6/ In accordance with sub-article (5) of this Article, the Collateral Registry may not require evidence of the existence of the grantor's authorization.

፳፫. ከአንድ በላይ በሆኑ የዋስትና ስምምነቶች ለተመሰረቱ የዋስትና መብቶች አንድ ማስታወቂያ በቂ ስለመሆኑ

አንድ መያዣ ሰጪ ከአንድ ዋስትና ያለው ግንዘብ ወያቂ ጋር በተፈራረመው አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆነ የዋስትና ስምምነት ላይ የተመሰረቱ የዋስትና መብቶችን በአንድ ማስታወቂያ መመዝገብ ይቻላል።

23. One Notice Sufficient for Security Rights Under Multiple Security Agreements

The registration of a single notice may relate to security rights created by the grantor under one or more than one security agreements with the same secured creditor.

፳፬. ለሕዝብ ተደራሽ ስለማድረግ

፩/ ማንኛውም ሰው በመያዣ መዝገቡ ማስታወቂያ ማስገባት የሚችለው በመያዣ መዝገቡ የተጠቃሚነት መለያ ኮድ ካለው እና በመመሪያ በሚወሰነው መሠረት የአገልግሎት ክፍያ ከከፈለ ነው።

፪/ የማሻሻያ ወይም የስረዛ ማስታወቂያ የሚቀርበው በተጠቃሚ መለያ ኮድ አማካኝነት እና በዚህ ክፍል መሠረት ማስታወቂያውን ለማቅረብ መብት ባለው ሰው አማካኝነት ብቻ ነው።

፫/ ማንኛውም ሰው የመረጃ ፍለጋ ቅጽ በሚጠይቀው መሠረት ለመያዣ መዝገቡ የፍለጋ ጥያቄ ማቅረብ ይችላል።

፬/ የመያዣ መዝገቡ የተጠየቀውን መረጃ የማይሰጥ ከሆነ የተከለከለበትን ምክንያት ለመዝጋቢው ወይም ለመረጃ ፈላጊው ወዲያውኑ መግለጽ አለበት።

24. Public Access

1/ Any person may submit a notice to the Collateral Registry, if that person has established a user account with the Registry; and has paid fee that shall be prescribed by directive.

2/ An amendment or cancellation notice may only be submitted through the user account and by the person that is authorized to submit such notice under this Part.

3/ Any person may submit a search request to the Collateral Registry, if that person uses the prescribed search request form.

4/ If access is refused, the Collateral Registry shall communicate the reason to the registrant or searcher without delay.

፳፭. የማስታወቂያ ምዝገባ ወይም የመረጃ ጥያቄን ውድቅ ስለማድረግ

፩/ የማስታወቂያ ምዝገባ ወይም የመረጃ ፍለጋ መስፈርት ቅፅ በሚጠይቀው መሠረትና ሥፍ ላይ ሙሞላት ያለበት አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆነ መረጃ ካልገባ የመያዣ መዝገቡ የማስታወቂያ ምዝገባውን ወይም ፍለጋውን አይቀበልም።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እንደተደነገገው ካልሆነ በስተቀር የመያዣ መዝገቡ የማስታወቂያ ምዝገባን ወይም የመረጃ ፍለጋ ጥያቄን ውድቅ ማድረግ አይችልም።

25. Rejection of the Registration of a Notice or a Search Request

1/ The Collateral Registry shall reject the registration of a notice or a search if no information is entered in one or more of the required designated fields.

2/ Except as provided in Sub Article (1) of this Article, the Collateral Registry may not reject the registration of a notice or a search request.

፫/ የማስታወቂያ ምዝገባ ወይም የመረጃ ፍለጋ ጥያቄ ውድቅ የተደረገ እንደሆነ የመያዣ መዝገቡ ምክንያቱን ለአስመዝጋቢው ወይም ለመረጃ ፈላጊው ወዲያውኑ ያሳውቃል።

3/ If the registration of a notice or a search request is rejected, the Collateral Registry shall communicate the reason to the registrant or searcher without delay.

፳፮. የመያዣ ምዝገባ ጽሕፈት ቤት ምርመራ እንዳያደርግ ስለመከልከሉ

የመያዣ ምዝገባ ጽሕፈት ቤት የማስታወቂያ ምዝገባ ወይም የፍለጋ ጥያቄ ወይም የማስታወቂያ ይዘትን መመርመር አይችልም።

26. No Verification by the Collateral Registry Office

The Collateral Registry Office may not conduct any scrutiny of the content of a notice or search request.

፳፯. ለመጀመሪያ ማስታወቂያ የሚያስፈልጉ መረጃዎች

፩/ የመጀመሪያ ማስታወቂያ የሚከተሉትን አማባብነት ባላቸው ቦታዎች የተሞሉ መረጃዎችን መያዝ ይኖርበታል፦

ሀ) በአንቀጽ ፳፰ መሠረት የመያዣ ሰጪውን መለያ ቁጥር እና ሙሉ ስም፣

ለ) በአንቀጽ ፳፱ መሠረት ዋስትና ያለውን ገንዘብ ጠያቂ ወይም የተወካዩን መለያ፣

ሐ) የመያዣ ሰጪውን እና ዋስትና ያለውን ገንዘብ ጠያቂ አድራሻ፣

መ) በአንቀጽ ፴ መሠረት መያዣውን የሚያብራራ መግለጫ፣

ሠ) ምዝገባው ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ፣ እና

ረ) ለስታትስቲካዊ ዓላማ ብቻ እንዲሰበሰብ በመመሪያ የሚወሰን ማንኛውም ሌላ መረጃ።

27. **Information Required in an Initial Notice**

1/ An initial notice shall contain the following information in the relevant designated field:

a) the identifier and name of the grantor in accordance with Article 28;

b) the identifier of the secured creditor or its representative in accordance with Article 29;

c) an address of the grantor and the secured creditor;

d) a description of the collateral in accordance with Article 30;

e) the period of effectiveness of the registration; and

f) any other information to be prescribed in the directive collected for statistical purpose only.

፪/ ከአንድ በላይ መያዣ ሰጪ ወይም ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ በሚኖርበት ጊዜ መረጃዎች ለእያንዳንዱ መያዣ ሰጪ ወይም ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ በተናጠል መሞላት ይኖርባቸዋል።

2/ If there is more than one grantor or secured creditor, the required information shall be entered separately for each grantor or secured creditor.

፳፰. የመያዣ ሰጪው መለያ

፩/ መያዣ ሰጪው የተፈጥሮ ሰው ከሆነ፦

ሀ) መለያው በመመሪያ የሚወሰን ልዩ የመታወቂያ ቁጥር፣ እና

28. **Grantor Identifier**

1/ Where the grantor is a natural person:

a) the grantor identifier is the unique identification number as prescribed in the directive; an

ለ) ስሙ የኢትዮጵያ ዜግነት ላለው ሰው የፀና ኦፊሴላዊ መታወቂያ ሠነድ ላይ የሰፈረው ስም ሲሆን፣ ኢትዮጵያዊ ዜግነት የሌለው የተፈጥሮ ሰው በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ የፀና ፓስፖርት ላይ የተገለፀው ስም ይሆናል።

፪/ መያዣ ሰጪው የሕግ ሰውነት ያለው ከሆነ:-

ሀ) መለያው በመመሪያ የሚወሰን ልዩ የመታወቂያ ቁጥር ፣ እና

ለ) ስሙ በማቋቋሚያ ሰነድ ወይም ሕግ ላይ የሰፈረ ስያሜ ይሆናል።

፳፱. ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መለያ

፩/ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ የተፈጥሮ ሰው በሚሆንበት ጊዜ መለያው በመመሪያ የሚወሰን የገንዘብ ጠያቂው ወይም የተወካዩ ሙሉ ስም ይሆናል።

፪/ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ የሕግ ሰውነት ያለው በሚሆንበት ጊዜ መለያው በመመሪያ የሚወሰን የገንዘብ ጠያቂው ወይም የተወካዩ ስም ይሆናል።

፴. <u>የዋስትና መግለጫ</u>

፩/ ለዋስትና የዋለ ወይም የሚውል ንብረት ማስታወቂያ ላይ በበቂ ሁኔታ እንዲለይ በሚያስችል መልኩ ተብራርቶ መገለጽ ይኖርበታል።

፪/ መግለጫው የመያዣ ሰጪውን ተንቀሳቃሽ ንብረት በሙሉ፣ ወይም በአንድ በተወሰነ ምድብ ውስጥ ያለ ሁሉንም ተንቀሳቃሽ ንብረት የሚይዝ መሆኑን ከገለጸ፣ ወይም በብዛት ወይም በስሌት ቀመር ካስቀመጠ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መስፈርትን ያሟላ ይሆናል።

b) the grantor name is the name as it appears in the most recent relevant official document issued to a citizen of Ethiopia or valid passport in case of natural persons who are not citizens of Ethiopia.

2/ Where the grantor is a legal person:

a) the grantor identifier is the unique identification number as prescribed in the directive, and

b) the grantor name is the name that appears in the most recent document or law constituting the legal person.

29. <u>Secured Creditor Identifier</u>

1/ Where the secured creditor is a natural person, the secured creditor identifier is the name of the secured creditor or its representative as prescribed in the directive.

2/ Where the secured creditor is a legal person, the secured creditor identifier is the name of the secured creditor or its representative as prescribed in the directive.

30. <u>Description of Collateral</u>

1/ The assets encumbered or to be encumbered shall be described in a notice in a manner that reasonably allows their identification.

2/ A description that indicates that the collateral consist of all of the grantor's movable property of all of the grantor's movable property within a particular category or a description by quantity or computational formula satisfies the standard of Sub Article (1) of this Article.

፫/ በማስታወቂያው ላይ ያለው መግለጫ በዋስትና ስምምነቱ ካለው መግለጫ ጋር አንድ ዓይነት ላይሆን ይችላል። ነገር ግን የማስታወቂያው መግለጫ በዋስትና ስምምነቱ ከተገለጸው የንብረት ዓይነት የሚበልጥ ሆኖ ከተገኘ ማስታወቂያው በትርፍነት በገለጻቸው ንብረቶች ላይ የዋስትና መብቱ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

፬/ በተመዘገበ ማስታወቂያ ውስጥ አንድን ንብረት መጥቀስ መያዣ ሰጪው በንብረቱ ላይ የባለቤትነት መብት እንዳለው ወይም ወደፊት እንደሚኖረው አያመላክትም።

፭/ የንግድ ዕቃ ካልሆነ በስተቀር መለያ ቁጥር ያለው መያዣ መለያ ቁጥር፣ በዓይነቱና በአምራቹ ስም መገለጽ አለበት።

፴፩. የማስታወቂያ ምዝገባ ተፈፃሚ ስለሚሆንበት ጊዜ

፩/ የመያዣ መዝገቡ ለመጀመሪያ ማስታወቂያ ልዩ የምዝገባ ቁጥር በመስጠት እና ይህንን ቁጥር መሠረት በማድረግ የተመዘገቡ የማሻሻያ ወይም የሰረዛ ማስታወቂያዎችን መጀመሪያ ከተመዘገበው ማስታወቂያ ጋር ያያይዛል።

፪/ የመጀመሪያ፣ የማሻሻያ እና የሰረዛ ማስታወቂያ መረጃዎች ተደራሽ እንዲሆኑ በመያዣ መዝገቡ ከተመዘገቡበት ቀን እና ሰዓት ጀምሮ ለህዝብ ክፍት ይሆናሉ።

፫/ የመያዣ መዝገቡ በማስታወቂያው ውስጥ ያለውን መረጃ ማስታወቂያው በቀረበበት ቅደም ተከተል ወዲያውኑ ወደመዝገቡ ያስገባል።

፬/ የመያዣ መዝገቡ ለመረጃ ፈላጊዎች ተደራሽ እንዲሆን በማስታወቂያው ውስጥ ያለው መረጃ ወደመዝገቡ የገባበትን ቀን እና ሰዓት ይመዘግባል።

3/ The description in the notice need not be identical to that in the security agreement. To the extent that the description in the notice exceeds the type of property described in the security agreement, the notice does not make effective against third parties security right in such assets.

4/ Reference to an asset in a registered notice does not imply or represent that the grantor presently or in the future will have right in the asset.

5/ Serial-numbered collateral shall be described by a serial number, the make, and the name of manufacturer, unless it is held as inventory.

31. Time of Effectiveness of the Registration of a Notice

1/ The Collateral Registry shall assign a unique registration number to a registered initial notice and associate all registered amendment or cancellation notices that contain that number with the registered initial notice.

2/ The registration of an initial, amendment and cancellation notice is effective from the date and time when the information in the notice is entered into the records of the Collateral Registry so as to be accessible to searchers.

3/ The Collateral Registry shall enter information in a notice into its records without delay after the notice is submitted and in the order in which each notice is submitted.

4/ The Collateral Registry shall record the date and time when the information in a notice is entered into its records so as to be accessible to searcher.

፴፪. የማስታወቂያ ምዝገባ የሚቆይበት ጊዜ

፩/ የመጀመሪያ ማስታወቂያ ተፈፃሚ ሆኖ የሚቆይበት ጊዜ መዝጋቢው በማስታወቂያው ላይ ይህንኑ ለማመልከት በተዘጋጀው ቦታ ላይ የገለጸው ሆኖ ከአሥር ዓመት መብለጥ የለበትም፡፡

፪/ የመጀመሪያ ማስታወቂያ ምዝገባ የተፈፃሚነት ጊዜ ከማብቃቱ በፊት ባሉት ስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ብቻ ምዝገባው እንዲራዘም በሚጠይቅበት ቦታ ላይ ከአሥር ዓመት የማይበልጥ የተጨማሪ ጊዜ በመመዝገብ ሊራዘም ይችላል፡፡

፫/ የመጀመሪያ ማስታወቂያ የተፈፃሚነት ጊዜ ከአንድ ጊዜ በላይ መራዘም ይችላል፡፡

፬/ የጊዜ ማሻሻያ የቀስትናው መራዘም የሚጀምርበትን ቀን ካላስቀመጠ ቀስትናው የተሻሻለው ማስታወቂያ ከሚያበቃበት ቀን ጀምሮ በማስታወቂያው ላይ ለተመለከተው ጊዜ ይራዘማል፡፡

፴፫. የተመዘገበ ማስታወቂያ ግልባጭ የመላክ ግዴታ

፩/ አንድ ማስታወቂያ እንደተመዘገበ የመያዣ ምዝገባ ሥርዓቱ ወዲያውኑ ምዝገባው መፈፀሙን የሚገልጽ ሰነድ ለመዝጋቢው የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

፪/ ምዝገባው መፈፀሙን የሚገልጸው ሰነድ ምዝገባው የተፈፀመበትን ቀን ፣ ሰዓት፣ እና የምዝገባውን ቁጥር የሚያሳዩ መረጃዎችን መያዝ ይኖርበታል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት መዝጋቢው የማስታወቂያውን ግልባጭ በአሥር የሥራ ቀናት ውስጥ ማስታወቂያውን በመያዣ ሰጪነት ለተመዘገበው ሰው መላክ ይኖርበታል፡፡

32. Period of Effectiveness of the Registration of a Notice

1/ The registration of an initial notice shall be effective for the period of time indicated by the registrant in the designated field of the notice that however may not exceed ten years.

2/ The period of effectiveness of the registration of an initial notice may be extended only within six months before its expiry by the registration of an amendment notice that indicates in the designated field a new period that may not exceed ten years.

3/ The period of effectiveness of the registration of an initial notice may be extended more than once.

4/ The registration of an amendment notice extends the period of effectiveness for the period indicated in the amendment notice beginning from the time the current period would have expired if the amendment notice had not been registered.

33. Obligation to Send a Copy of a Registered Notice

1/ Without delay after the registration of a notice, the Collateral Registry shall provide to the registrant a copy of the information in a registered notice.

2/ The information in a registered notice shall indicate the date and time the registration became effective and the registration number.

3/ Within ten working days after the registrant receives a copy of the information in the notice in accordance with Sub Article (1) of this Article, the registrant shall send it to the person identified in the registered notice as the grantor.

፴፬. የማሻሻያ ወይም የስረዛ ማስታወቂያ የመመዝገብ መብት

፩/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪) እንደተጠበቀ ሆኖ በተመዘገበ የመጀመሪያ ማስታወቂያ ላይ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ተብሎ የተጠቀሰው ሰው ምዝገባውን አስመልክቶ የማሻሻያ ወይም የስረዛ ማስታወቂያ መመዝገብ ይችላል።

፪/ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ማንነት የሚቀይር የማሻሻያ ማስታወቂያ ከተመዘገበ በኋላ የማሻሻያ ወይም የስረዛ ማስታወቂያ መመዝገብ የሚችለው በማሻሻያ ምዝገባው ላይ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ሆኖ የተጠቀሰው ሰው ብቻ ነው።

፫/ በተመዘገበ የመጀመሪያ ወይም የማሻሻያ ማስታወቂያ ላይ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ተብሎ የተጠቀሰው ሰው ላይፈቅድ የተመዘገበ የማሻሻያ ወይም የስረዛ ማስታወቂያ ተፈፃሚ ሊሆን አይችልም።

፴፭. በማሻሻያ ወይም በስረዛ ማስታወቂያ ላይ መካተት ያለበት መረጃ

፩/ አንድ የማሻሻያ ማስታወቂያ ለዚሁ ተብሎ በተለየ ቦታ ላይ፣

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፩(፩) መሠረት በመያዣ መዝገቡ የተሰጠን ልዩ የምዝገባ ቁጥር፣ እና

ለ) የሚፈጸመረውን ወይም የሚለወጠውን መረጃ፣

መያዝ አለበት።

፪/ የማሻሻያ ማስታወቂያው በተመዘገበ ማስታወቂያ ውስጥ ያለ መረጃ አንዱን ወይም ከአንድ በላይ የሆነውን ሊመለከት ይችላል።

፫/ አንድ የስረዛ ማስታወቂያ ለመጀመሪያ ማስታወቂያው የተሰጠውን ልዩ የምዝገባ ቁጥር ለዚሁ በተለየ ቦታ ላይ ማሳየት ይኖርበታል።

34. Right to Register an Amendment or Cancellation Notice

1/ subject to Sub Article (2) of this Article, the person identified in a registered initial notice as the secured creditor may register an amendment or cancellation notice relating to that notice.

2/ Upon registration of an amendment notice changing the person identified in a registered initial notice as the secured creditor. only the person identified in the amendment notice as the secured creditor may register an amendment or cancellation notice.

3/ The registration of an amendment or cancellation notice is ineffective unless authorized by the person identified in the registered initial or amendment notice as the secured creditor.

35. Information Required in an Amendment and Cancellation Notice

1/ An amendment notice shall contain in the relevant designated field:

a) the unique registration number assigned by the Collateral Registry pursuant to Article 31(1) ; and

b) the information to be added or otherwise modified.

2/ An amendment notice may relate to one or more than one item of information in a registered notice.

3/ A cancellation notice shall contain in the designated field the unique registration number assigned to the registered initial notice to which the cancellation relates.

፴፮. አስገዳጅ የማሻሻያ ወይም የሰረዛ ማስታወቂያ ምዝገባ

፩/ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ፦

ሀ) የማሻሻያ ማስታወቂያው መያዣ ሰጪው ከፈቀደው በላይ መረጃ የያዘ እንደሆነ፣ ወይም

ለ) የተመዘገበው ማስታወቂያ የተወሰነ የዋስትና መያዣን የሚያሰርዝ ሆኖ ከተሻሻለ፣

የማሻሻያ ማስታወቂያ ማስመዝገብ አለበት፡፡

፪/ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ፦

ሀ) መያዣ ሰጪው የመጀመሪያ ማስታወቂያ እንዲመዘገብ ካልፈቀደ፣

ለ) መያዣ ሰጪው የመጀመሪያው ምዝገባ እንዲፈጸም ፈቃዱን ከሰጠ በኋላ የሰጠውን ፈቃድ ካነሳ እና የዋስትና ስምምነት ካልተፈረመ፣ ወይም

ሐ) ማስታወቂያው የሚመለከተው የዋስትና መብት ቀሪ እንደሆነ እና ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ለመያዣ ሰጪው ክፍያ የመፈፀም ተጨማሪ ግዴታ ከሌለበት፣

የሰረዛ ማስታወቂያው መመዝገብ አለበት፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፭(ሀ) እና ፮(ሀ) የተገለጸው ሁኔታ ሲኖር ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ግዴታውን ለመወጣት ክፍያ መጠየቅ ወይም መቀበል አይችልም፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ከተደነገጉት ሁኔታዎች አንዱ ከተሟላ መያዣ ሰጪው ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ የማሻሻያ ወይም የሰረዛ ማስታወቂያ እንዲያስመዘግብ በጽሑፍ መጠየቅ የሚችል ሲሆን፣ ገንዘብ ጠያቂው ይህንን ለማድረግ ምንም ዓይነት ክፍያ ወይም ወጪ መጠየቅ ወይም መቀበል አይችልም፡፡

36. Compulsory Registration of an Amendment or Cancellation Notice

1/ The secured creditor shall register an amendment notice if:

a) the registered notice to which it relates contains information that exceeds the scope of the grantor's authorization; or

b) the security agreement to which the registered notice relates has been revised to delete some collateral.

2/ The secured creditor shall register a cancellation notice if:

a) the registration of an initial notice was not authorized by the grantor;

b) the registration of an initial notice was authorized by the grantor but the authorization has been withdrawn and no security agreement has been concluded; or

c) the security right to which the notice relates has been extinguished and the secured creditor has no further commitment to provide value to the grantor.

3/ In cases under Sub Articles 1(a) and (2) (a) the secured creditor may not charge or accept any fee or expense for complying with its obligation.

4/ If any of the conditions set out in Sub Articles (1) and (2) of this Article are met, the grantor is entitled to request the secured creditor in writing to register an amendment or cancellation notice and the secured creditor may not charge or accept any fee or expense.

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ክመያዣ ሰጪው በጽሐፍ በደረሰው ጥያቄ መሠረት በአሥር የሥራ ቀናት ውስጥ ክልፈፀመ መያዣ ሰጪው የማሻሻያ ወይም የስረዛ ማስታወቂያው በመያዣ ምዝገባ ጽሕፈት ቤት በኩል እንዲመዘገብ መጠየቅ ይችላል።

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) መሠረት የሚጠየቅን የማሻሻያ ወይም የስረዛ ማስታወቂያ የመያዣ ምዝገባ ጽሕፈት ቤት ወዲያውኑ መዝግቦ ዋስትና ላለው ገንዘብ ጠያቂ ግልባጩ የሚደረግ ተገቢ ትዕዛዝ መስጠት አለበት።

፴፯. <u>የመፈለጊያ መስፈርት</u>

ለሕዝብ ክፍት በሆነው የመያዣ መዝገብ ውስጥ ያለን መረጃ፦

፩/ የመያዣ ሰጪውን መለያ፣ ወይም

፪/ የመያዣን መለያ ቁጥር፣

በመጠቀም መፈለግ ይችላል።

፴፰. <u>ስለፍለጋ ውጤት</u>

፩/ በዚህ ክፍል የተገለጹትን መስፈርቶች የሚሟላ የፍለጋ ጥያቄ ሲቀርብ የመያዣ ምዝገባ ሥርዓቱ ወዲያውኑ፦

ሀ) ፍለጋው የተከናወነበትን ቀን እና ሰዓት፣

ለ) እያንዳንዱ ከፍለጋው መሥፈርት ጋር ሙሉ በሙሉ የሚመሳሰል መረጃ፣ ወይም

ሐ) ከፍለጋው መሥፈርት ጋር ሙሉ በሙሉ የሚመሳሰል መረጃ አለመገኘቱን፣

የሚያሳይ ምላሽ ይሰጣል።

፪/ ተቃራኒ ማስረጃ እስክሊለ ድረስ በመያዣ መዝገቡ ለፍለጋ ጥያቄ የተሰጠ ማስረጃ ስለ ፍለጋው ይዘት ማረጋገጫ ይሆናል።

5/ If the secured creditor does not comply with the grantor's written request referred to in Sub Article (4) of this Article within ten working days after its receipt, the grantor is entitled to seek the registration of an amendment or cancellation notice through the Collateral Registry Office.

6/ An amendment or cancellation notice in accordance with Sub Article (5) of this Article shall be registered by the Collateral Registry Office without delay upon the issuance of the relevant order with a copy of the order to the secured creditor.

37. <u>Search Criteria</u>

A public search of a record may be conducted according to:

1/ the identifier of the grantor; or

2/ the serial number of the collateral.

38. <u>Search Results</u>

1/ Upon submission of a search request that satisfies the requirements of this Part, the Collateral Registry shall, without delay, provide a search result that

a) indicates the date and time when the search was performed;

b) sets forth all information in each registered notice that contains information matching the search criterion exactly; or

c) indicates that no registered notice contains information matching the search criterion exactly.

2/ A search result issued by the Collateral Registry is proof of its contents in the absence of evidence to the contrary.

ሸ፱. ማስታወቂያ ውስጥ የገባ የአስፈላጊ መረጃ ስህተት

፩/ የመያዣ ሰጪው መለያ ላይ የተፈጠረ ስህተት የማስታወቂያ ምዝገባው ተፈፃሚ እንዳይሆን ያደርጋል፡፡

፪/ በአንድ የመያዣ ሰጪ መለያ ላይ የተፈጠረ ስህተት በሌሎች በትክክል የተገለጹ መያዣ ሰጪዎች ላይ ምዝገባው ተፈፃሚ እንዳይሆን አያደርግም፡፡

፫/ ከመያዣ ሰጪው መለያ በስተቀር በሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች ላይ የተፈጠረ ስህተት አንድ ምክንያታዊ የሆነ መረጃ ፈላጊን በከባዱ የሚያሳስት አስከልሆነ ድረስ ምዝገባው ተፈፃሚ እንዳይሆን አያደርግም፡፡

፬/ ለስታቲስቲክስ ተብሎ በመመሪያ እንዲመዘገቡ በተጠየቁ መረጃዎች ላይ የተፈጠረ ስህተት የምዝገባውን ተፈፃሚነት አያስቀርም፡፡

፭/ በአንድ የዋስትና መግለጫ ላይ የተፈጠረ ስህተት ሌላ በበቂ ሁኔታ የተገለፀ መያዣ የማስታወቂያ ምዝገባ ተፈፃሚነትን አያስቀርም፡፡

፮/ የመለያ ቁጥር ያለው ዋስትናን መለያ ቁጥር መሳሳት ምዝገባውን በንብረቱ ገዢ እና ተከራይ ረገድ ተፈፃሚነት እንዳይኖረው ያደርጋል፡፡

ሸ፲. ከምዝገባ በኋላ የመያዣ ሰጪው መለያ መለወጥ

፩/ መያዣ ሰጪው መለያውን ከመቀየሩ ቢያንስ ከአሥር ቀናት በፊት ስለለውጡ ዋስትና ላለው ገንዘብ ጠያቂ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

፪/ ከምዝገባ በኋላ የመያዣ ሰጪው መለያ ከተለወጠ፡ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ስለለውጡ ማስታወቂያ ከደረሰው በኋላ ባሉት አሥር ቀናት ውስጥ እና የተመዘገበው ማስታወቂያ የተፈፃሚነት ጊዜ ከማብቃቱ በፊት የማሻሻያ ማስታወቂያውን ካስመዘገበ፡ ማስታወቂያው የሚመለከተው የዋስትና

39. Error in Required Information Entered in a Notice

1/ An error in the grantor identifier renders the registration of the notice ineffective.

2/An error in the grantor identifier does not render the registration of the notice ineffective with respect to other grantors correctly identified in the notice.

3/ An error in required information other than the grantor's identifier does not render the registration ineffective unless the error would seriously mislead a reasonable searcher.

4/ Any error in the statistical information prescribed by directive may not affect the effectiveness of the registration.

5/ An error in the description of the collateral does not render the registration of the notice ineffective with respect to other collateral sufficiently described.

6/ An error in the serial number of the serial-numbered collateral renders the registration ineffective as against a buyer or lessee of that asset.

40. Post-Registration Change of Grantor Identifier

1/ The grantor shall notify the secured creditor of the changes in the grantor identifier at least ten days before the change.

2/ If the grantor's identifier changes after a notice is registered and the secured creditor registers an amendment notice indicating the new identifier of the grantor within ten days after the change notification is received but before the expiry of the period of effectiveness of the registered notice, the security right to

መብት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ያለው ተፈፃሚነት ወንቶ የሚቆይ ሲሆን ከለውጡ በፊት ከተወዳዳሪ መብት ጠያቂዎች የነበረው ቀደምትነትም የተጠበቀ ይሆናል።

፫/ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከተው ጊዜ ካበቃ በኋላ የማሻሻያ ማስታወቂያ ካስመዘገበ፦

ሀ) ማስታወቂያ የተመዘገበበት ወይም የመያዣ ሰጪው መለያ ከተለወጠ በኋላ ነገር ግን ማሻሻያው ከመመዝገቡ በፊት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ የሆነ የዋስትና መብት፣ የማሻሻያ ማስታወቂያው ከሚመለከተው የዋስትና መብት ቀደምትነት ይኖረዋል፣

ለ) ከመያዣ ሰጪው መለያ ለውጥ በኋላ ነገር ግን ከማሻሻያ ማስታወቂያው ምዝገባ በፊት መያዣውን የገዛ፣ የተከራየ ወይም የመጠቀም ፈቃድ የተሰጠው ሰው የማሻሻያ ማስታወቂያ መብቱን ከሚመለከተው የዋስትና መብት ነፃ ሆኖ ያገኛል።

which the notice relates remains effective against third parties and retains the priority it had over the right of competing claimants before the change.

3/ If the secured creditor registers an amendment notice after the expiration of the time period indicated in Sub Article (2) of this Article:

a) the security right with respect to which a notice is registered or which is otherwise made effective against third parties after the change in the grantor's identifier but before the registration of the amendment notice has priority over the security right to which the amendment notice relates;

b) a person that buys, leases or licenses the collateral after the change in the grantor's identifier but before the registration of the amendment notice acquires its right free of the security right to which the amendment notice relates.

፵፩. ከምዝገባ በኋላ ስለሚተላለፍ መያዣ

የተመዘገበና በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ የሆነ የዋስትና መያዣ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ መያዣው ለሌላ ሰው ከተሰጠ ወይም ከተላለፈ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ያለው የተፈፃሚነት መብት ወንቶ የሚቆይ ሲሆን፣ ከተፎካካሪ መብት ጠያቂዎች ያለው ቀደምትነትም የተጠበቀ ነው።

41. **Post-Registration Transfer of the Collateral**

A security right in collateral that was made effective against third parties by registration of a notice remains effective against third parties and retains its priority over the right of competing claimants after the collateral is sold or otherwise transferred by the grantor to a transferee that acquires its right subject to the security right.

፵፪. በመያዣ መዝገብ ውስጥ ስለተመዘገበው መረጃ ተአማኒነት

፩/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፮(፮) እንደተጠበቀ ሆኖ የመያዣ ምዝገባ ጽሕፈት ቤት ማንኛውም የተመዘገበ ማስታወቂያ ውስጥ ያለን መረጃ ማሻሻል ወይም መሰረዝ አይችልም።

42. **Integrity of Information in the Collateral Registry**

1/ Without prejudice to Article 36 (6) the Collateral Registry Office may not amend or delete information contained in any registered notice.

፪/ የመያዣ ምዝገባ ጽሕፈት ቤት በመዝገቡ ውስጥ የሚገኝ መረጃን ጠብቆ የማቆየት እና መረጃው ሲጠፋ ወይም ሲጐዳ መልሶ የማደራጀት ግዴታ አለበት።

2/ The Collateral Registry Office shall preserve information contained in its records and reconstruct it in the event of loss or damage.

፵፫. <u>መረጃን ከመያዣ መዝገብ እና ከማህደር ስለማስወገድ</u>

43. <u>Removal of Information from the Collateral Registry and Archival</u>

፩/ የመያዣ ምዝገባ ጽሕፈት ቤት ለሕዝብ ክፍት በሆነው የምዝገባ ማስታወቂያ ውስጥ ያለን መረጃ የማስታወቂያው ምዝገባ የተፈፃሚነት ጊዜ ሲያበቃ ማውጣት አለበት።

1/ The Collateral Registry Office shall remove information in a registered notice from its public records only upon the expiry of the period of effectiveness of the registration of a notice.

፪/ የመያዣ ምዝገባ ጽሕፈት ቤት ለሕዝብ ክፍት ከሆነው መዝገብ የተወገደ መረጃን በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፯ መሠረት መልሶ ሊገኝ በሚያስችል መልኩ ለአሥር ዓመት ማስቀመጥ ይኖርበታል።

2/ The Collateral Registry Office shall archive information removed from its public records for ten years in a manner that enables the information to be retrieved by the Collateral Registry in accordance with Article 37.

፵፬. <u>የመያዣ ምዝገባ ጽሕፈት ቤት የተጠያቂነት ወሰን</u>

44. <u>Limitation of Liability of the Collateral Registry Office</u>

የመያዣ ምዝገባ ጽሕፈት ቤት በሌሎች ሕጎች ተጠያቂነት የሚኖረው፦

Any liability that the Collateral Registry Office may have under other laws is limited for loss or damage caused by:

፩/ ለመረጃ ፈላጊው የተሰጠ ምላሽ ወይም ለመዝጋቢው ተሰጥቶ በተመዘገበ ማስታወቂያ ግልባጭ ውስጥ ስህተት በመፈፀም ወይም መረጃ ባለማካተት፣

1/ an error or omission in a search result issued to a searcher or in a copy of a registered notice provided to the registrant;

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፮ (፭) እና (፮) መሠረት በዋስትና መዝገብ ውስጥ መረጃ ሲመዘገብ ስህተት በመፈፀም ወይም መረጃ ባለማስገባት ወይም ከመዝገቡ ውስጥ በስህተት መረጃ በማውጣት፣

2/ In accordance with Article 36 (5) and (6) an error or omission in entering or failing to enter information in the records or in erroneously removing information from the records;

፫/ የመያዣ መዝገቡ ለመዝጋቢው የተመዘገበ ማስታወቂያ ግልባጭ ባለመስጠቱ፣ ወይም

3/ a failure of the Collateral Registry to send a copy of the registered notice to the registrant; or

፬/ ለመዝጋቢው ወይም ለመረጃ ፈላጊው ሀሰተኛ ወይም አሳሳች መረጃ በመስጠት፣ ለደረሰ ኪሣራ ወይም ጉዳት ነው።

ክፍል አምስት

የቀዳሚነት መብት

፵፭. ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ የቀዳሚነት መብት

፩/ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ከሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች ይልቅ የቀዳሚነት መብት አለው።

፪/ በኪሣራ ሕግ ቡቲቃራኒው ካልተደነገገ በስተቀር የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተፈጻሚነት በኪሣራ ወይም በሂሳብ ማጣራት ጊዜም ይቀጥላል።

፵፮. በአንድ የመያዣ ሰጪ ስለተፈጠሩ ተወዳዳሪ የዋስትና መብቶች

፩/ የዚህ ክፍል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው አንድ መያዣ ሰጪ በተመሳሳይ ዋስትና ላይ በፊጠራቸው የዋስትና መብቶች መካከል ያለው የቀዳሚነት መብት የሚወሰነው ዋስትና የተመሰረተበት ጊዜ ቅደም ተከተል ከግምት ሳይገባ በምዝገባቸው ቅደም ተከተል ነው።

፪/ የዋስትና ውል ከመፈፀሙ ወይም በታሳቢ ሀብት ላይ መያዣ ሰጪው የማስያዝ መብት ወይም ስልጣን ከማግኘቱ በፊት የተመዘገበ የዋስትና መብት ቀዳሚነት የሚወሰነው በምዝገባው ቅደም ተከተል መሠረት ነው።

፵፯. በተለያዩ መያዣ ሰጪዎች ስለተፈጠሩ ተወዳዳሪ የዋስትና መብቶች

አንድ መያዣ ሰጪ መያዣውን ያገኘው በዚሁ መያዣ ላይ ቀደም ብሎ በሌላ ሰው የተመሰረተ የዋስትና መብት እንደተጠበቀና በሦስተኛ ወገኖች ላይም ተፈጻሚ ከሆነ፣ በመያዣው ላይ የተመሰረተው መብት ቀደም ብሎ በሌላው ሰው ከተመሰረተው የዋስትና መብት የበታች ነው።

4/ the provision of false or misleading information to a registrant or searcher.

PART FIVE

PRIORITIY RIGHT

45. PRIORITY OF THE SECURED Creditor

1/ The secured creditor shall have priority over other creditors.

2/ unless otherwise provided in the insolvency law, Sub Article (1) of this Article shall continue during insolvency or liquidation.

46. Competing Security Right Created by the Same Grantor

1/ Subject to the provisions of this Part, priority among competing security rights created by the same grantor in the same collateral is determined according to the order of registration, without regard to the order of creation, of the security right.

2/ The priority of a security right with respect to which a notice has been registered in the Collateral Registry before the conclusion of a security agreement or, in the case of a security right in a future asset, before the grantor acquires right in the asset or the power to encumber it, is determined according to the time of registration.

47. Competing Security Rights Created by Different Grantors

A security right created by a grantor is subordinate to a security right in the same collateral created by another person if the grantor acquired the collateral subject to the security right created by the other person and made effective against third parties before the grantor acquired the collateral.

፵፰. የዋስትና መብት መኖሩን ማወቅ ውጤት የሌለው ስለመሆኑ

ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ የዋስትና መብት መኖሩን ማወቁ በዚህ አዋጅ መሠረት ያለውን የቀዳሚነት መብት አያሳጣውም።

፵፱. በሶስተኛ ወገኖች ላይ ተፈጻሚ የሆነ የዋስትና መንገድ በሚለወጥበት ጊዜ ስለሚኖሩ ተወዳዳሪ የዋስትና መብቶች

በዚህ ክፍል ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በስተቀር በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈጻሚ የነበረ የዋስትና መብት የተመሠረተበት መንገድ ሲለወጥ የጊዜ ክፍተት እስከሌለው ድረስ የቀዳሚነት መብቱ የተጠበቀ ይሆናል።

፶. ታሳቢ ብድር እና ታሳቢ መያዣ

፩/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፭ እንደተጠበቀ ሆኖ ቀዳሚ የዋስትና መብት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ከሆነ በኋላ የተገቡ ግዴታዎችን ጨምሮ ሁሉንም ዋስትናቸው የተጠበቁ ግዴታዎችን ይሸፍናል።

፪/ ከምዝገባው በፊት ወይም በኋላ በመያዣ ሰጪው የተገኘ ወይም የተፈጠረ ቢሆንም ቀዳሚ የዋስትና መብት በመያዣ መዝገቡ በማስታወቂያ ተለይተው የተመዘገቡ ዋስትናዎችን በሙሉ ይሸፍናል።

፶፩. በተያያዥ ገቢ ላይ ስለሚኖር ቀዳሚ የዋስትና መብት

የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፮ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፬ መሠረት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈጻሚ የሆነ የተያያዥ ገቢ ዋስትና መብት ከተወዳዳሪ የዋስትና መብት ይልቅ የገቢው ምንጭ በሆነው ዋስትና ላይ በተመሠረተው የቀዳሚነት መብት መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል።

48. Irrelevance of Knowledge of the Existence of a Security Right

Knowledge of the existence of a security right on the part of a secured creditor does not affect its priority under this Proclamation.

49. Competing Security Rights in the Case of a Change in the Method of Third-Party Effectiveness

Unless otherwise provided in this Part, the priority of a security right is not affected by a change in the method by which it is made effective against third parties, provided there is no time gap during which the security right is not effective against third parties.

50. Future Advances and Future Collateral

1/ Subject to Article 55, the priority of a security right extends to all secured obligations, including obligations incurred after the security right became effective against third parties.

2/ The priority of a security right covers all collateral described in a notice registered in the Collateral Registry, whether they are acquired by the grantor or come into existence before or after the time of registration.

51. Priority of a Security Right in Proceeds

Subject to Article 58, a security right in proceeds that is effective against third parties under Article 14 has the same priority over a competing security right as the security right in the collateral from which the proceeds arose.

፶፪. በውህድ ወይም በምርት ውስጥ የተቀላቀሉ ግዑዝ ሀብቶች ላይ ስለሚኖር ቀዳሚ የዋስትና መብት

፩/ የተቀላቀሉ ወይም የተዋሃዱ ዕቃዎች ከአንድ ለሚበልጥ የዋስትና መብት ከዋሉ ዕቃዎቹ ከመቀላቀላቸው በፊት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ የሆነው የዋስትና መብት ዕቃዎቹ ከተቀላቀሉ በኋላ ከሚመሰረት የዋስትና መብት በፊት የቀዳሚነት መብት አለው።

፪/ የተቀላቀሉ ወይም የተዋሃዱ ዕቃዎች ከአንድ ለሚበልጥ የዋስትና መብቶች ከዋሉና በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ከሆኑ የመብቶቹ ቀዳሚነትና ዋጋ ዕቃዎቹ በተዋሃዱበት ጊዜ ባለው መሠረት ይሆናል።

52. Priority of Security Right in Corporeal Assets Commingled in a Mass or Product

1/ If more than one security right extends to commingled goods, a security right that is effective against third parties before the goods become commingled has priority over a security right that is not effective against third parties at the time the collateral becomes commingled goods.

2/ If more than one security right in commingled goods is effective against third parties, the security rights rank equally in proportion to the value of the collateral at the time it became commingled goods.

፶፫. በማይንቀሳቀስ ንብረት ተጓዳኝ ላይ ስለሚኖር ቀዳሚ የዋስትና መብት

፩/ የዋስትና መብት የማይንቀሳቀስ ንብረት ተጓዳኝ በሆኑ ወይም ሊሆኑ በሚችሉ ግዑዝ ሀብቶች ላይ ሊመሠረት ወይም ሊቀጥል ይችላል። ሆኖም መብቱ በመደበኛ የግንባታ ዕቃዎች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም።

፪/ በዚህ አዋጅ መሠረት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ የሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት ተጓዳኝ የዋስትና መብት በሌሎች ህጎች ከተመሠረቱና ተፈፃሚ ከሆኑ ተወዳዳሪ መብቶች ይልቅ የቀዳሚነት መብት አለው።

53. Priority of Security Right in Accessories to Immovable

1/ A security right may be created in corporeal assets that are accessories to immovable or may continue in corporeal assets that become accessories to immovable. A security right, however, may not be created in ordinary building materials incorporated into an immovable.

2/ A security right made effective against third parties in an accessory to immovable under this Proclamation has priority over a competing right created and made effective against third parties under other applicable laws.

፶፬. መያዣውን የገዛ፣ የተላለፈለት፣ የተከራየ ወይም እንዲጠቀም ፈቃድ የተሰጠው ሰው መብቶች

፩/ የዋስትና መብት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ሆኖ እያለ መያዣው በሽያጭ ወይም በሌላ ሁኔታ ከተላለፈ፣ ከተከራየ ወይም የመጠቀም ፈቃድ ከተሰጠ ገዢው ወይም መብቱ የተላለፈለት፣ የተከራየ ወይም የተፈቀደለት በዚህ አንቀጽ እንደተደነገገው ካልሆነ በስተቀር የንብረቱ ባለመብት የሚሆነው በላዩ ላይ ያለው የዋስትና መብት እንደተጠበቀ ሆኖ ነው።

54. Rights of Buyers or Other Transferees, Lessees or Licensees of Collateral

1/ If the collateral is sold or otherwise transferred, leased or licensed while the security right in that asset is effective against third parties, the buyer or other transferee, lessee or licensee acquires its right subject to the security right except as provided in this Article.

፪/ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ንብረቱን ከዋስትና ነፃ ሆኖ እንዲተላለፍ የፈቀደ እንደሆነ መያዣው በግዢ ወይም በሌላ ሁኔታ የተላለፈለት ሰው መብቱን ከዋስትናው ነፃ በሆነ ሁኔታ ያገኛል።

፫/ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መያዣውን ከዋስትናው ነፃ በሆነ ሁኔታ እንዲያከራይ ወይም የመጠቀም ፈቃድ እንዲሰጥ ለመያዣ ሰጪው የፈቀደ እንደሆነ ተከራዩ ወይም የመጠቀም ፈቃድ የተሰጠው ሰው መብት በዋስትናው መብት አይታወክም።

፬/ በሻፊ መደበኛ የንግድ ሥራ ውስጥ ገዢው የሸያጭ ውሉን በተዋዋለበት ወቅት ንብረቱ ለመያዣ መዋሉንና ሻፊ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂን መብት የጣሰ መሆኑን ካላወቀ በግዢው የሚያገኛቸው መብቶች ከዋስትናው ነፃ ናቸው።

፭/ በአከራዩ መደበኛ የንግድ ሥራ ውስጥ ተከራዩ የኪራይ ውሉን በተዋዋለበት ወቅት ንብረቱ ለመያዣ መዋሉንና ኪራዩ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂን መብት የጣሰ መሆኑን ካላወቀ በኪራዩ የሚያገኛቸው መብቶች ከዋስትናው ነፃ ናቸው።

፮/ በፈቃድ ሰጪው መደበኛ የንግድ ሥራ ውስጥ ፈቃድ ተቀባዩ አዕምሯዊ ንብረትን ለመጠቀም የፈቃድ ውሉን በተዋዋለበት ወቅት አዕምሯዊ ንብረቱ ለዋስትና መዋሉንና ፈቃዱ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂን መብት የሚጥስ መሆኑን ካላወቀ በፈቃዱ የሚያገኛቸው መብቶች ከዋስትናው ነፃ ናቸው።

2/ A buyer or other transferee of the collateral acquires its right free of the security right, if the secured creditor authorizes the sale or other transfer of the asset free of the security right.

3/ The right of a lessee or licensee of the collateral is not affected by a security right if the secured creditor authorizes the grantor to lease or license the asset unaffected by the security right.

4/ A buyer of corporeal collateral sold in the ordinary course of the seller's business acquires its rights free of the security right, provided that, at the time of the conclusion of the sale agreement, the buyer does not have knowledge that the sale violates the rights of the secured creditor under the security agreement.

5/ The rights of a lessee of corporeal collateral leased in the ordinary course of the lessor's business are not affected by the security right, provided that, at the time of the conclusion of the lease agreement, the lessee does not have knowledge that the lease violates the right of the secured creditor under the security agreement.

6/ The rights of a non-exclusive licensee of intellectual property licensed in the ordinary course of the licensor's business are not affected by the security right, provided that, at the time of the conclusion of the license agreement, the licensee does not have knowledge that the license violates the right of the secured creditor under the security agreement.

፯/ አንድን መያዣ የገዛ ወይም በሌላ መንገድ የተላለፈለት ሰው መብቶቹን ከዋስትናው ነፃ በሆነ ሁኔታ ካገኛቸው ቀጣዩ ገዢ ወይም መብቱ የሚተላለፍለት ሰው መብቶቹን የሚያገኘው ከዋስትናው ነፃ በሆነ ሁኔታ ነው።

፰/ አንድ በዋስትና የተያዘ ግዑዝነት ያለው ወይም የሌለውን ሀብት ከዋስትና ነፃ የተከራየ ወይም ፈቃድ የተቀበለ ከሆነ የቀጣዩ ተከራይም ሆነ ፈቃድ ተቀባይ መብቶች በዋስትናው አይታወኩም።

፶፭. <u>በህግ ወይም በፍርድ የግንዘብ ጠያቂነት መብት የተሰጠው ሰው መብቶች</u>

፩/ በህግ ወይም በፍርድ ገንዘብ ጠያቂነት መብት የተሰጠው ሰው የዋስትና መብቱ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ከመሆኑ አስቀድሞ በመያዣ መዝገብ ውስጥ ይህንኑ ካስመዘገበ መብቱ ቀዳሚነት ይኖረዋል።

፪/ በህግ ወይም በፍርድ ገንዘብ ጠያቂነት መብት የተሰጠው ሰው ማስታወቂያ ከመመዝገቡ አስቀድሞ የዋስትና መብቱ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ከሆነ ይኼው መብት ቀዳሚነት ይኖረዋል።ነገር ግን ይህ የቀዳሚነት መብት:-

ሀ) በህግ ወይም በፍርድ ገንዘብ ጠያቂነት መብት የተሰጠው ሰው በመያዣ መዝገቡ ውስጥ ስለመመዝገቡ ማስታወቂያ ከሰጠበት ጊዜ ጀምሮ በሰላሳ የሥራ ቀናት ውስጥ፣ ወይም

ለ) መጠኑ አስቀድሞ የተወሰነ ወይም ዋስትና ባለው ገንዘብ ጠያቂ ተስይቶ በተቀመጠ ቀመር መሠረት በተወሰነ ገንዘብ ወይም የማይሻር ግዴታ በተገባለትና በህግ ወይም በፍርድ ገንዘብ ጠያቂነት መብት የተሰጠው ሰው ለመያዣ ሰጪው ማስታወቂያ ከመስጠቱ በፊት፣

በተሰጠ ብድር ላይ ብቻ የተወሰነ ይሆናል።

7/ If a buyer or other transferee of corporeal collateral acquires its rights free of a security right, any subsequent buyer or other transferee also acquires its rights free of that security right.

8/ If the rights of a lessee of a corporeal collateral or licensee of incorporeal collateral are not affected by the security right, the rights of any sub-lessee or sub-licensee are also unaffected by that security right.

55. <u>Rights of Non-Consensual Creditors</u>

1/ The right of a non-consensual creditor has priority over a security right if, before the security right is made effective against third parties, the non-consensual creditor has registered a notice in the Collateral Registry.

2/ If a security right is made effective against third parties before the non-consensual creditor registers a notice, the security right has priority but that priority is limited to credit extended by the secured creditor:

a) within thirty working days from the time the secured creditor received a notification from the non-consensual creditor that the non-consensual creditor has registered a notification in the Collateral Registry; or

b) pursuant to an irrevocable commitment in a fixed amount or an amount to be fixed pursuant to a specified formula of the secured creditor to extend credit, if the commitment was made before the secured creditor received a notice from the non-consensual creditor that the non-consensual creditor had registered a notice.

፫/ በመደበኛ የንግድ ሥራ ሂደት ለሚቀርቡ የአገልግሎት ወይም የእቅርቦት፡ ክፍያን ወይም አፈጻጸምን ለማረጋገጥ ዕቃዎችን ለዋስትና በይዞታ ሥር ለማቆየት የሚያስችል የዋስትና መብት እስካለ ድረስ ይህ የይዞታ መብት ቀዳሚነት ይኖረዋል።

3/ A possessory lien on goods which secures payment or performance of an obligation for services or materials furnished with respect to goods by a person in the ordinary course of the person's business has priority over a security right in the goods as long as the holder of the possessory lien remains in possession of the goods.

፶፮. ከተገኘ የዋስትና መብት ጋር የሚወዳደር ሌላ የዋስትና መብት

፩/ በሸማች ዕቃዎች፣ በመሣሪያዎች እና በአዕምሯዊ ንብረቶች ላይ የተገኘ የዋስትና መብት መያዣ ሰጪው ከመሠረተው ሌላ ተወዳዳሪ የዋስትና መብት ቀዳሚነት የሚኖረው፡-

ሀ) የተገኘ የዋስትና መብት ያለው ግንዘብ ጠያቂ ንብረቱን በይዞታው ሥር ካደረገ፣ ወይም

ለ) መያዣ ሰጪው ሀብቱን በይዞታው ሥር ባደረገ ወይም አዕምሯዊው ንብረት ላይ መብት ባገኘ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ የተገኘ የዋስትና መብት ማስታወቂያ የተመዘገበ እንደሆነ፣

ነው።

፪/ በንግድ ዕቃ ላይ የተገኘ የዋስትና መብት መያዣ ሰጪው ከመሠረተው ሌላ ተወዳዳሪ የዋስትና መብት ቀዳሚነት የሚኖረው፡-

ሀ) የተገኘ የዋስትና መብት ያለው ግንዘብ ጠያቂ መያዣውን በይዞታው ሥር ካደረገ፣ ወይም

ለ) መያዣ ሰጪው ሀብቱን በይዞታው ሥር ከማድረጉ ቀደም ብሎ የተገኘ የዋስትና መብት ማስታወቂያ የተመዘገበ ከሆነ፣ እና

56. Acquisition Security Right Competing with Non-Acquisition Security Right

1/ An acquisition security right in consumer goods, equipment, or intellectual property has priority as against a competing non-acquisition security right created by the grantor provided that:

a) the acquisition secured creditor is in possession of the asset; or

b) a notice with respect to the acquisition security right is registered in the Collateral Registry within seven working days after the grantor obtains possession of the asset or acquires a right in intellectual property.

2/ An acquisition security right in inventory has priority as against a competing non-acquisition security right created by the grantor if:

a) the acquisition secured creditor is in possession of the asset; or

b) a notice with respect to the acquisition security right is registered in the Collateral Registry before the grantor obtains possession of the asset; and

ሐ/ የተገኘ የዋስትና መብት ያለው ሰው በተመሳሳይ ዓይነት መያዣ ላይ ማስታወቂያ ለመዘገበና ዋስትና ላለው ገንዘብ ጠያቂ በመያዣው የዋስትና መብት እንዳለው ወይም ለማግኘት ማቀዱን ካስታወቀው፡

ነው፡፡

፶፯. የተገኙ የዋስትና መብቶች ተወዳዳሪነት

፩/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ተወዳዳሪ በሆኑ የተገኙ የዋስትና መብቶች መካከል ቀዳሚነት የሚወሰነው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፮ መሠረት ነው፡፡

፪/ ከሻጭ፣ ከአከራይ ወይም ከፈቃድ ሰጪ የተገኘ የዋስትና መብት ዋስትና ካለው ተወዳዳሪ ገንዘብ ጠያቂ መብት ቀዳሚነት ይኖረዋል፡፡

፶፰. በተያያዥ ገቢ ላይ የተገኘ የዋስትና መብት

፩/ በመሣሪያ ላይ የተገኘ የዋስትና መብት ካለ በሁለቱ ተያያዥ ገቢ ላይ የሚኖር የቀዳሚነት መብት ከተገኘ የዋስትና መብት ጋር ተመሳሳይ ይሆናል፡፡

፪/ በአዕምሯዊ ንብረት ወይም በንግድ ዕቃ ላይ የተገኘ ቀዳሚ የዋስትና መብት ካለ በንብረቱ ተያያዥ ገቢ ላይም የቀዳሚነት መብቱ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ ሆኖም ገቢው ተሰብሳቢ ሂሳብ የሚተላለፍ የገንዘብ ሰነድ፣ የንግድ ወረቀት ወይም ወደ ተቀማጭ ሂሳብ ከሚገባ ገንዘብ ላይ ክፍያ የመጠየቅ መብት ከሆነ ቀዳሚነቱ አይሙሬም፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ላይ የተመለከተው የቀዳሚነት መብት የሚወሰነው የተገኘ የዋስትና መብት ያለው ገንዘብ ጠያቂ ተያያዥ ገቢው ከመገኘቱ በፊት በመያዣ መዝገብ ውስጥ ማስታወቂያ ስለመመዝገቡ በህግ ወይም በፍርድ ገንዘብ ጠያቂነት መብት ለተሰጣቸው ገንዘብ ጠያቂዎች ያስታወቃቸው እንደሆነ ነው፡፡

c) the holder of the acquisition security right notifies a secured creditor that has registered a notice against the collateral of the same kind that it has or intends to obtain an acquisition security right.

57. Competing Acquisition Security Rights

1/ Subject to Sub Article (2) of this Article, the priority between competing acquisition security rights is determined according to Article 46.

2/ An acquisition security right of a seller, lessor or licensor has priority over a competing acquisition security right of a secured creditor.

58. Acquisition security Right in Proceeds

1/ In the case of an acquisition security right in equipment, a security right in proceeds has the same priority as the acquisition security right.

2/ In the case of an acquisition security right in inventory or intellectual property, a security right in proceeds has the same priority as the acquisition security right, except where the proceeds take the form of receivables, negotiable instruments, or rights to payment of funds credited to a deposit account.

3/The priority of a security right in proceeds under Sub Article (2) of this Article is conditional on the acquisition secured creditor notifying non-acquisition secured creditors with a security right in the same kind of asset as the proceeds that, before the proceeds arose, the acquisition secured creditor registered a notice in the Collateral Registry.

፶፱. ከውሀድ ወይም ከምርት ጋር በተቀላቀሉ ግዑዝ ሀብቶች ላይ የተገኘ የዋስትና መብት

ውሀድን ወይም ምርትን በሚሸፍንና በግዑዝ ሀብት ላይ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ሆኖ የተገኘ የዋስትና መብት በተመሳሳይ መያዣ ሰጪ ከተመሠረተ ሌላ የዋስትና መብት ይልቅ ቀዳሚነት አለው።

፷. የቀዳሚነት መብትን ስለማሳለፍ

፩/ ማንኛውም ሰው በማናቸውም ጊዜ በዚህ አዋጅ የተሰጠውን የቀዳሚነት መብት ለማንኛውም ተወዳዳሪ የዋስትና ባለመብት ተጠቃሚውን ወገን ተዋዋይ ማድረግ ሳያስፈልግ የቅድሚያ መብቱን አሳልፎ መስጠት ይችላል።

፪/ የቀዳሚነት መብትን ማሳለፍ መብቱን ካሳለፈው ሰው እና ከተጠቃሚው ውጭ የሌሎች ተወዳዳሪ ባለመብቶችን አያውክም።

፷፩. የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች

፩/ በዋስትና ከተመዘገበና በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚነት ካለው የሚተላለፍ የገንዘብ ሰነድ የዋስትና መብት ይልቅ ሰነዱን በይዞታው ሥር ለዋስትና ያደረገ ባለመብት ቀዳሚነት አለው።

፪/ በዋስትና የተያዘና መብቱ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ሆኖ የሚተላለፍ የገንዘብ ሰነድን ገዥው ወይም በህግ የተላለፈለት ሰው ከዋስትናው ነፃ በሆነ መንገድ ሊያገኝ የሚችለው፦

ሀ) ሰነዶቹን በንግድ ሕጉ መሠረት እንደያዘ የሚቆጠር ከሆነ፣ ወይም

59. Acquisition Security Right in Corporeal Assets Commingled in a Mass or Product

An acquisition security right in a corporeal asset that extends to a mass or product effective is against third parties has priority over a non-acquisition security right granted by the same grantor in the mass or product.

60. Subordination of Priority Right

1/ A person may at any time subordinate the priority of its right under this Proclamation in favor of any competing claimant without the need for the beneficiary to be a party to the subordination.

2/ Subordination does not affect the right of competing claimants other than the person subordinating its priority and the beneficiary of the subordination.

61. Negotiable Instruments

1/ A security right in a negotiable instrument that is made effective against third parties by possession of the instrument has priority over a security right in the instrument that is made effective against third parties by registration of a notice in the Collateral Registry.

2/ A buyer or other consensual transferee of an encumbered negotiable instrument acquires its right free of a security right that is made effective against third parties by registration of a notice in the Collateral Registry if the buyer or other consensual transferee:

a) qualifies as a holder in due course under the Commercial Code; or

ለ) ሰነዶቹን በይዞታው ሥር ካደረገ እና ሽያጩ ወይም ዝውውሩ ዋስትና ያለው ግንዘብ ጠያቂ መብት እንደሚጥስ ባለማወቅ ዋጋ ከከፈለ፡

ነው።

፷፪. በተቀማጭ ሂሳብ ውስጥ ከሚገባ ግንዘብ ክፍያን የመጠየቅ መብት

፩/ ወደ ተቀማጭ ሂሳብ ከሚገባ ግንዘብ ላይ ክፍያ የመጠየቅ የዋስትና መብት ያለውና ሂሳቡ በይዞታው ሥር የሚገኝ ባለመብት በሌላ ማንኛውም መንገድ ከሚገኝና በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ከሚሆን የዋስትና መብት ይልቅ ቀዳሚነት አለው።

፪/ ወደ ተቀማጭ ሂሳብ ውስጥ ከሚገባ ግንዘብ ክፍያ የመጠየቅ የዋስትና መብት ያለው የፋይናንስ ተቋም ከሆነ፣ የዋስትና መብት ያለው ሌላ ክፍያ ጠያቂ የሂሳቡ ባለይዞታ በመሆን በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ካደረገው ተወዳዳሪ የዋስትና መብት ውጭ በሌላ ማንኛውም መንገድ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ከሆነው ተወዳዳሪ የዋስትና መብት ይልቅ ቀዳሚነት ይኖረዋል።

፫/ በቁጥር ስምምነት አማካኝነት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ በሆነና ወደ ተቀማጭ ሂሳብ ከሚገባ ግንዘብ ክፍያ የመጠየቅ መብት ላይ ያለ የዋስትና መብት፦

ሀ) ከፋይናንስ ተቋሙ የዋስትና መብት፣ ወይም

ለ) የሂሳቡ ባለይዞታ የሆነ ዋስትና ያለው ግንዘብ ጠያቂ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ካደረገው የዋስትና መብት፣

በስተቀር ከሌላ ተወዳዳሪ የዋስትና መብት ቀዳሚነት ይኖረዋል።

b) takes possession of the negotiable instrument and gives value without knowledge that the sale or other transfer is in violation of the right of the secured creditor under the security agreement.

62. Right to Payment of Funds Credited to a Deposit Account

1/ A security right in a right to payment of funds credited to a deposit account that is made effective against third parties by the secured creditor becoming the account holder has priority over a competing security right that is made effective against third parties by any other method.

2/ A security right in a right to payment of funds credited to a deposit account with respect to which the secured creditor is the financial institution has priority over a competing security right made effective against third parties by any method other than by the secured creditor becoming the account holder.

3/ A security right in a right to payment of funds credited to a deposit account that is made effective against third parties by a control agreement has priority over a competing security right except:

a) a security right of the financial institution; or

b) a security right that is made effective against third parties by the secured creditor that has become the account holder.

፬/ ወደ ተቀማጩ ሂሳብ ከሚገባ ገንዘብ ክፍያ የመጠየቅ መብት ያላቸውና በቁጥጥር ስምምነት አማካኝነት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ የሆኑ ተወዳዳሪ የዋስትና መብቶች መካከል ቅዳሚነት የሚወሰነው የቁጥጥር ስምምነት የተደረገበትን ጊዜ መሠረት በማድረግ ነው።

4/ The order of priority among competing security right in a right to payment of funds credited to a deposit account that are made effective against third parties by the conclusion of control agreement is determined on the basis of the time of conclusion of the control agreement.

፭/ ወደ ተቀማጩ ሂሳብ ከሚገባ ገንዘብ ክፍያ የመጠየቅ የዋስትና መብት ካለው ሰው ይልቅ አንድ የፋይናንስ ተቋም የተበዳሪውን ዕዳ ለማቻቻል ያለው መብት ቅዳሚነት አለው፣ ሆኖም ይህ የቅዳሚነት መብት የሂሳቡ ባለይዞታ በመሆን የዋስትና መብቱን በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ያደረገ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂን የዋስትና መብት አይጥስም።

5/ A financial institution's right to set off obligations owed to it by the grantor has priority as against a security right in the right to payment of funds credited to the deposit account, except a security right that is made effective against third parties by the secured creditor becoming the account holder.

፮/ በመያዣ ሰፈኒው ፈቃድ ወይም አማካኝነት ከአንድ ተቀማጩ ሂሳብ ላይ ገንዘብ የተላለፈለት ሰው ይህ ዝውውር ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መብትን የሚጥስ መሆኑን ካላወቀ ገንዘቡን ከዋስትና ነፃ በሆነ መንገድ ያገኛል።

6/ A transferee of funds from a deposit account pursuant to a transfer initiated or authorized by the grantor acquires its right free of a security right in the right to payment of funds credited to the deposit account, unless the transferee has knowledge that the transfer violates the right of the secured creditor under the security agreement.

፷፫. ገንዘብ

በዋስትና መብት ከተያዘ ገንዘብ ላይ ዝውውር የተፈፀመለት ሰው ገንዘቡን ከዋስትና ነፃ በሆነ መንገድ ሊያገኝ የሚችለው ዝውውሩ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መብትን የሚጥስ መሆኑን ካላወቀ ብቻ ነው።

63. Money

A transferee that obtains possession of money that is subject to a security right acquires its right free of the security right, unless that person has knowledge that the transfer violates the right of the secured creditor under the security agreement.

፷፬. ተላላፊ ሰነድ እና በሰነዱ የሚሸፈኑ ግዑዝ ሀብቶች

፩/ የሚተላላፍ ሰነድን በይዞታ ሥር በማድረግ ሰነዱ በሚሸፍነው ንብረት ላይ ተፈፃሚ የሆነ የዋስትና መብት በሌላ ማንኛውም መንገድ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ከሆነው ተወዳዳሪ የዋስትና መብቱ ቅዳሚነት ይኖረዋል።

64. Negotiable Document and Corporeal Assets Covered by that Document

1/ A security right in a corporeal asset made effective against third parties by possession of the negotiable document covering that asset has priority over a competing security right made effective against third parties by any other method.

፪/ በዋስትና የተያዘ ተላላፊ ሰነድ የተላለፈለት ሰው ሰነዱን ተቀብሎ በይዞታው ሥር ካደረገ፣ የንብረት ሽያጩ ወይም ዝውውሩ ሌላ ዋስትና ያለው ግንዘብ ጠያቂ መብትን እንደሚጎዳ ባለማወቅ ዋጋ ከፍሎበት ከሆነ፣ መብቱ በሰነዱ ወይም በሰነዱ በተሸፈኑ ግዑዝ ሀብቶች ላይ ካለ እና በዚህ አዋጅ መሠረት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ከሆነው የዋስትና መብት ነፃ ሆኖ ያገኛል።

2/ A transferee of an encumbered negotiable document that obtains possession of the document and gives value without knowledge that the sale or other transfer is in violation of the right of the secured creditor under the security agreement, acquires its right free of a security right in the document and the corporeal assets covered thereby that is made effective against third parties under this Proclamation.

፷፭. ሴኩሪቲዎች

65. Securities

፩/ በሰነድ የተደገፉ ሴኩሪቲዎችን በይዞታው ሥር በማድረግ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ያደረገ የዋስትና መያዣ መብት፣ መያዣ ሰጪው በሴኩሪቲዎች ላይ ከፈጠረውና ማስታወቂያ ለማስመዝገብ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ካደረገው ሌላ ተፎካካሪ የዋስትና መብት ቀዳምትነት ይኖረዋል።

1/ A security right in certificated securities made effective against third parties by the secured creditor's possession of the certificate has priority over a competing security right created by the same grantor in the same securities made effective against third parties by registration of a notice in the Collateral Registry.

፪/ በአውጪው ወይም እርሱን በመወከል በኤሌክትሮኒክ ሴኩሪቲዎች ላይ ስለዋስትና መያዣ መብት በተዘጋጀ መዝገብ ላይ መግለጫ በመጻፍ ወይም ዋስትና ያለው ግንዘብ ጠያቂን ስም እንደባለመብት መመዝገብ በሴኩሪቲዎቹ ላይ በሌላ ማንኛውም መንገድ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ከሆነው የዋስትና መብት ይልቅ በምዝገባው የተገኘው መብት ቀዳሚነት ይኖረዋል።

2/ A security right in electronic securities made effective against third parties by a notation of the security right or registration of the name of the secured creditor as the holder of the securities in the books maintained for that purpose by or on behalf of the issuer has priority over a security right in the same securities made effective against third parties by any other method.

፫/ የቁጥጥር ስምምነት በመፈራረም በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ የሆነ የኤሌክትሮኒክ ሴኩሪቲዎች የዋስትና መብት በእነዚሁ ሴኩሪቲዎች ላይ ማስታወቂያ በማስመዝገብ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ከሆነው የዋስትና መብት ይልቅ ቀዳሚነት ይኖረዋል።

3/ A security right in electronic securities made effective against third parties by the conclusion of a control agreement has priority over a security right in the same securities made effective against third parties by registration of a notice in the Collateral Registry.

፬/ በቁጥጥር ስምምነቶች አማካኝነት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ የሆኑ ተመዳዳሪ የኤሌክትሮኒክ ሴኩሪቲዎች ላይ የዋስትና መብቶች መካከል ቀዳሚነት የሚወሰነው ስምምነቶቹ የተደረጉበትን ጊዜ መሠረት በማድረግ ነው።

፭/ በሰነድ የተደገፉ ሴኩሪቲዎችን በይዞታው ሥር ያደረገ ወይም የኤሌክትሮኒክ ሴኩሪቲዎች ላይ መብት ያገኘና መብቱ የተላለፈለት ሰው ሽያጩ ወይም ዝውውሩ በዋስትና ውሉ መሠረት ዋስትና ያለው ሌላ ግንዘብ ጠያቂን መብት እንደሚጥስ ባለማወቅ ዋጋ ከፍሎበት ከሆነ መብቱን ከዋስትናው ነፃ ሆኖ ያገኛል።

ክፍል ስድስት

የተዋዋይ ወገኖች እና ሦስተኛ ወገን ተገዳጆች መብትና ግዴታ

፷፮. መያዣውን በይዞታው ሥር ካደረገ ሰው የሚጠበቅ ግዴታ

አንድ የመያዣ ሰጪ ወይም ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ በይዞታው ሥር የሚገኝ መያዣን ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ መጠበቅ አለበት።

፷፯. ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ግዴታ

የዋስትና መብት በሚቋረጥበት ጊዜ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ፦

፩/ በይዞታው ሥር ያለውን ዋስትና ለመያዣ ሰጪው ይመልስለታል፤

፪/ ያስመዘገበውን የዋስትና ማስታወቂያ በአንቀጽ ፴፮ (፪) (ሐ) መሠረት ይሰርዛል፤

፫/ በቁጥጥር ስምምነት መሠረት ስምምነቱን ያነሳል።

፷፰. መያዣውን የመጠቀም፣ ወጪው እንዲተካ የማድረግ እና የመቆጣጠር መብት

፩/ ዋስትናው በይዞታው ሥር የሆነ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ፦

4/ The order of priority among competing security rights in electronic securities that are made effective against third parties by the conclusion of control agreements are determined on the basis of the time of conclusion of the control agreements.

5/ A transferee of securities who takes possession of the certificated security or acquires right in an electronic security and gives value without knowledge that the sale or other transfer is in violation of the right of the secured creditor under the security agreement acquires its right free of a security right.

PART SIX

RIGHT AND OBLIGATION OF THE PARTIES AND THIRDPARTY OBLIGORS

66. Obligation of a Person in Possession to Exercise Reasonable Care

A grantor or secured creditor in possession of the collateral shall exercise reasonable care to preserve the asset.

67. Obligation of a Secured Creditor

Upon termination of a security right in the collateral, the secured creditor:

1/ in possession shall return it to the grantor;

2/ not in possession shall register cancellation notice as provided in Article 36 (2) (c);

3/ in control shall release it.

68. Right to use, be Reimbursed for Expenses and Inspect the Collateral

1/ A secured creditor in possession of the collateral:

ሀ) የመድን፣ የግብር እና ሌሎች ክፍያዎችን ጨምሮ ሀብቱን ለመጠበቅ ያወጣው ተገቢ የሆነ ወጪ እንዲተካለትና ወጪውም ዋስትናው በተጠበቀው ግዴታ ላይ እንዲታከል የማድረግ መብት አለው፣

ለ) መያዣውን በአግባቡ በመጠቀም፣ ከመያዣውም ይገኛል ተብሎ ስምምነት የተደረገበትን ገቢ ዋስትና ለተገባለት ግዴታ ክፍያ ማዋል ይችላል።

፪/ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ በመያዣ ሰጪው ወይም በሌላ ሰው ይዞታ ሥር ያለን መያዣ የመቆጣጠር መብት አለው።

፷፱. መረጃ የማግኘት መብት

፩/ መያዣ ሰጪው ዋስትና የተገባለትን ግዴታ ወይም መያዣውን በሚመለከት መረጃ እንዲሰጠው ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂን መጠየቅ ይችላል።

፪/ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መረጃ እንዲሰጥ ጥያቄ በቀረበለት በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ለመያዣ ሰጪው ወይም መያዣ ሰጪው ለወከለው ሰው:-

ሀ) ዋስትና ተገብቶለት ነገር ግን ስላልተከፈለ ግዴታ የሂሳብ መግለጫ፣

ለ) ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ በየትኛው ዋስትና ላይ የዋስትና መብት እንዳለው የሚያመለክት መግለጫ፣ ወይም

ሐ) ዋስትና ተገብቶለት ነገር ግን ስላልተከፈለ ግዴታ ሂሳብ የሚገልጽና የዋስትና መያዣ መብቱ ተፈጻሚ የሚሆንበትን ዋስትና የሚያመለክት መግለጫ፣

መስጠት አለበት።

a) has the right to be reimbursed and add to the secured obligation any reasonable expenses it incurs for the preservation of the asset, including the cost of insurance, payment of taxes and other charges;

b) may reasonably use the collateral and apply the agreed sum generated from the service for the payment of the secured obligation.

2/ A secured creditor has the right to inspect the collateral in the possession of the grantor or another person.

69. Right to Obtain Information

1/ A grantor is entitled to request the secured creditor to provide information with regard to the secured obligation or the collateral.

2/ Within five working days after receipt of a request for information, a secured creditor shall provide to the grantor or a person designated by the grantor:

a) statement of account that provides an accounting of the unpaid obligation secured by the collateral;

b) statement indicating the collateral in which the secured creditor claims a security right; or

c) statement that both provides an accounting of the unpaid obligation secured by the collateral and identifies the collateral subject to a security right.

ፍ. የተሰብሳቢ ሂሳብ ባለዕዳ ስለሚደረግለት ጥበቃ

በዚህ አዋጅ በተቃራኒው ካልተደነገገ በስተቀር በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የዋስትና መብት መመሥረት ለሂሳቡ መነሻ በሆነው ዋናው ውል የተካተቱ የክፍያ ሁኔታዎችን ጨምሮ የባለዕዳውን መብትና ግዴታ ከእርሱ ፈቃድ ውጭ አያውክም።

70. Protection of the Debtor of the Receivable

Except as otherwise provided in this Proclamation, the creation of a security right in a receivable does not affect the right and obligation of the debtor of the receivable, including the payment terms contained in the contract giving rise to the receivable, without its consent.

ፍ፩. በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የዋስትና መብትንና ክፍያን ስለማሳወቅ

፩/ በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የዋስትና መብት ተፈፃሚነት የሚኖረው ባለዕዳው በዋስትና የተያዘውን ተሰብሳቢ ሂሳብና ዋስትና ያለው ጉንዘብ ጠያቂን በሚገባ የለየ ማስታወቂያ ሲደርሰው ነው።

፪/ በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የተመሠረተ የዋስትና መብት ከማስታወቂያ በኋላ የሚፈጠር ተሰብሳቢ ሂሳብንም ሊያካትት ይችላል።

፫/ የተሰበሳቢ ሂሳቡ ባለዕዳ ስለተመሰረተው የዋስትና መብት ማስታወቂያ እስከሚደርሰው ድረስ በዋናው ውል መሠረት የክፍያ ግዴታውን ይፈፅማል። ባለዕዳው ማስታወቂያው ከደረሰው በኋላ ከግዴታው ነፃ የሚሆነው ዋስትና ላለው ገንዘብ ጠያቂ ክፍያን በመፈፀም ወይም በማስታወቂያው ወይም በገንዘብ ጠያቂው በጽሑፍ ተቃራኒ ማሳወቂያ ከተሰጠው በኃ ነው።

፬/ የተሰብሳቢ ሂሳቡ ባለዕዳ በተሰብሳቢ ሂሳቡ ላይ ስለተመሰረተና ከአንድ በላይ የሆነ የዋስትና መብት ማስታወቂያ ከመያዣ ሰጪው ከደረሰው መጀመሪያ በደረሰው ማስታወቂያ መሠረት ክፍያ በመፈፀም ከግዴታው ነፃ ይሆናል።

71. Notification of a Security Right and Payment of a Receivable

1/ Notification of a security right in a receivable is effective when received by the debtor of the receivable if it reasonably identifies the encumbered receivable and the secured creditor.

2/ Notification of a security right in a receivable may relate to receivables arising after notification.

3/ Until the debtor of the receivable receives notification of a security right in a receivable, it is discharged by paying in accordance with the original contract. After the debtor of the receivable receives notification of a security right in a receivable, it is discharged only by paying the secured creditor or, if otherwise instructed in the notification or subsequently by the secured creditor in a writing received by the debtor of the receivable.

4/ If the debtor of the receivable receives notification of more than one security right in the same receivable created by the same grantor, it is discharged by paying in accordance with the first notification received.

ሯ/ የተሰብሳቢ ሂሳቡ ባለዕዳ ዋስትና ያለውን ገንዘብ ጠያቂ በተሰብሳቢው ሂሳብ ላይ የዋስትና መብት ለመኖሩ ተገቢ በሆነ ጊዜ ውስጥ በቂ ማረጋገጫ እንዲያቀርብ ሊጠይቀው ይችላል። ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ በዚህ መሠረት እስከሚፈፅም ድረስ የተሰብሳቢ ሂሳቡ ባለዕዳ ስለዋስትና መብቱ ማስታወቂያ ቢደርሰውም እንኳን ለመያዣ ሰጪው ክፍያ በመፈፀም ግዴታውን መወጣት ይችላል።

ፎ፪. <u>የተሰብሳቢ ሂሳብ ባለዕዳ መቃወሚያዎችና የማቻቻል መብት</u>

፪/ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ የተሰብሳቢ ሂሳብ ባለዕዳን በዋስትና የተያዘውን ተሰብሳቢ ሂሳብ እንዲከፍል ጥያቄ ሲያቀርብ የተሰብሳቢ ሂሳቡ ባለዕዳ በገንዘብ ጠያቂው ላይ በመቃወሚያነት፡-

ሀ) ለተሰብሳቢ ሂሳቡ መመስረት ምክንያት ከሆነው ውል የሚመነጩ መቃወሚያ ዎችንና የማቻቻል መብትን ወይም የዚሁ አካል ሌላ ግብይትን በመጥቀስ የዋስትና መብቱ እንዳልተመሰረተ፡

ለ) ባለዕዳው ስለዋስትና መብቱ ማስታወቂያ በደረሰው ጊዜ ሊጠቀምበት የሚችለውን የማቻቻያ መብት፡

ማንሳት ይችላል።

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቢኖርም፡ የተሰብሳቢ ሂሳብ ባለዕዳ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱ ስምምነት ተጥሷል የሚል የመከላከያ ወይም መብት የማቻቻል ጥያቄ በማንሳት መያዣ ሰጪው በተሰብሳቢ ሂሳቡ ላይ ያለውን ዋስትና የመመስረት መብት በማንኛውም ሁኔታ ሊገድብበት አይችልም።

5/ The debtor of the receivable is entitled to request the secured creditor to provide within a reasonable period of time adequate proof that the security right in a receivable has been created. Until the secured creditor complies, the debtor of the receivable may discharge its obligation by paying the grantor, even if the debtor of the receivable has received a notification of a security right.

72. <u>Defenses and Right of Set-Off of the Debtor of the Receivable</u>

1/ In a claim by the secured creditor against the debtor of the receivable for payment of the encumbered receivable, the debtor of the receivable may raise against the secured creditor:

a) all defenses and right of set-off arising from the contract giving rise to the receivable or any other contract that was part of the same transaction of which the debtor of the receivable could avail itself as if the security right had not been created and the claim were made by the grantor;

b) any other right of set-off that was available to the debtor of the receivable at the time it received notification of the security right.

2/ Despite Sub Article (1) of this Article, the debtor of the receivable may not raise as a defense or right of set-off against the grantor breach of an agreement referred to in Article 9 limiting in any way the grantor's right to create the security right.

፫/ የተሰብሳቢ ሂሳብ ባለዕዳ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከቱ መቃወሚያዎችንና የማቻቻል መብትን ዋስትና ባለው ግንዘብ ጠያቂ ላይ ላለማንሳት ከመያዣ ሰጪው ጋር በጽሑፍ ለመስማማት ይችላል። ሆኖም ዋስትና ከተሰጠው ግንዘብ ጠያቂ የማጭበርበር ተግባር የሚመነጩ ወይም በራሱ ችሎታ ማጣት ላይ የተመሠረቱ መቃወሚያዎችን አያስቀርም።

3/The debtor of the receivable may agree with the grantor in a signed writing not to raise against the secured creditor the defenses and right of set-off referred to in Sub Article (1) of this Article. The debtor of the receivable may not waive defenses arising from fraudulent acts on the part of the secured creditor or based on the incapacity of the debtor of the receivable.

፸፫. <u>ተሰብሳቢ ሂሳብ የተመሠረተበትን ዋና ውል ስለማሻሻል</u>

በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ ስለተመሠረተ የዋስትና መብት ማስታወቂያ ከመሰጠቱ በፊት በመያዣ ሰጪውና በባለዕዳው መካከል የተፈረመ የዋናው ውል ማንኛውም ማሻሻያ ዋስትና ያለው ግንዘብ ጠያቂ መብትን የሚነካ ቢሆንም ተፈፃሚ ነው፣ ዋስትና ያለው ግንዘብ ጠያቂም በተሻሻለው ውል መሠረት የሚመለከተውን መብት ያገኛል።

73. <u>Modification of the Original Contract of Receivables</u>

Any modification to the original contract concluded before notification of a security right in a receivable between the grantor and the debtor of the receivable that affects the secured creditor's right is effective as against the secured creditor and the secured creditor acquires corresponding right.

፸፬. <u>የተሰብሳቢ ሂሳብ ባለዕዳ የፈፀማቸውን ክፍያዎች ስለማስመለስ</u>

በመያዣ ሰጪው ወይም በውል የተሰብሳቢ ሂሳብን ሙሉ በሙሉ ያስተላለፈ ሰው የተሰብሳቢው ሂሳብ መነሻ የሆነውን ውል መፈፀም ባለመቻሉ ባለዕዳው ለመያዣ ሰጪው ወይም ዋስትና ላለው ግንዘብ ጠያቂ የከፈለውን ግንዘብ የማስመለስ መብት አይሰጠውም።

74. <u>Recovery of Payments Made by the Debtor of the Receivable</u>

The failure of the grantor or, in the case of an outright assignment of a contractual receivable the assignor of the receivable to perform the contract giving rise to a receivable, does not entitle the debtor of the receivable to recover from the secured creditor a sum paid by the debtor of the receivable to the grantor or the secured creditor.

፸፭. <u>ከሕዝብ ተቀማጭ ገንዘብ የመሰብሰብ ፈቃድ ከተሰጣቸው የፋይናንስ ተቋማት ተጻራሪ የሆነ መብት</u>

፩/ በተቀማጭ ሂሳብ ውስጥ ገቢ ከሚደረግ ገንዘብ ላይ ክፍያ የማግኘት የዋስትና መብት ሲመሰረት፣ ከሕዝብ ተቀማጭ ገንዘብ የመሰብሰብ ፈቃድ ያለው የፋይናንስ ተቋም ለዋስትና መብቱ መመሥረት ይሁንታውን ካልሰጠ በስተቀር መብቱና ግዴታው የተጠበቀ ሲሆን ለሦስተኛ ወገኖችም ስለሂሳቡ ማንኛውንም መረጃ እንዲሰጥ አይገደድም።

75. <u>Right as Against the Financial Institution Authorized to Receive Deposits from the Public</u>

1/ The creation of a security right in a right to payment of funds credited to a deposit account does not affect the right and obligation of the financial institution authorized to receive deposits from the public with which that deposit account is maintained without its consent, nor does it obligate the financial institution to provide any information about that deposit account to third parties.

፪/ በፋይናንስ ተቋሙ ውስጥ ከተከፈተ የተቀማጭ ሂሳብ ላይ ተቋሙ ያለውን ማንኛውም የማቻቻል መብትና በተቀማጭ ሂሳቡ ገቢ ከሚደረግ ገንዘብ ክፍያ የማግኘት የዋስትና መብቱን አያውክም፡፡

2/ Any right of set-off that the financial institution may have are not affected by any security right that the bank may have in a right to payment of funds credited to a deposit account maintained with the financial institution.

ክፍል ሰባት
የዋስትና መብት ማስከበር

PART SEVEN
ENFORCEMENT OF A SECURITY RIGHT

፸፮. ከግዴታ አለመፈፀም በኋላ ስለሚኖሩ መብቶች

76. Post-Default Rights

፩/ ከግዴታ አለመፈጸም በኋላ በመያዣው ላይ ያለ መብትን መጠቀም ዋስትና የተገባለት ግዴታ የማስፈጸም መብት መጠቀምን አያስቀርም፣ ከግዴታ አለመፈጸም በኋላ ዋስትና የተገባለት ግዴታ የማስፈጸም መብትን መጠቀም በመያዣው ላይ ያለ መብት መጠቀምን አይከለክልም፡፡

1/ The exercise of a post-default right with respect to the collateral does not prevent the exercise of a post-default right with respect to the secured obligation, the exercise of a post-default right with respect to the secured obligation does not prevent the exercise of a post-default right with respect to the collateral.

፪/ መያዣ ሰጪው እና ዋስትና የተገባለት ግዴታን የመክፈል ወይም የመፈጸም ሃላፊነት ያለበት ሌላ ማንኛውም ሰው በዚህ ክፍል ድንጋጌዎች ሥር ያሉትን መብቶች በራሱ መተው ወይም በስምምነት ማሻሻል አይችልም፡፡

2/ The grantor and any other person that owes payment or other performance of the secured obligation may not waive unilaterally or vary by agreement any of its rights under the provisions of this Part prior to default.

፫/ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ በዚህ ክፍል ሥር ያሉትን መብቶች በቅን ልቦና እና ተገቢ በሆነ የንግድ አሠራር መሠረት መጠቀም አለበት፡፡

3/ The secured creditor shall exercise its remedies under this Part in good faith and in a commercially reasonable manner.

፸፯. ባልተከበረ ግዴታ ላይ ዳኝነት ስለመጠየቅ

77. Relief for Non-Compliance

፩/ ማንኛውም የዚህ ክፍል ድንጋጌዎች ባለመከበራቸው ምክንያት ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መብቱ በሌላ ሰው የተነካበት ከሆነ ዳኝነት እንዲሰጠው ለፍርድ ቤት ማመልከት የሚችል ሲሆን፣ ይህም በተፋጠነ ሥነ ሥርዓት መዳኘትን ይጨምራል፡፡

1/ The secured creditor whose right is affected by the non-compliance of another person with the provisions of this Part is entitled to apply for relief to a court, including relief in the form of expeditious proceedings.

፪/ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ በአንቀጽ ፹፪(፬) ላይ የተደነገጉትን የፍትሐብሔር የፈረቃ ሽያጭ አፈፃፀም ሥነ ሥርዓቶች በመተላለፍ በባለዕዳው ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት ተጠያቂነት አለበት፡፡

2/ The secured creditor shall be liable for any damage it causes to the debtor in the process of selling by auction in violation of the relevant provisions of the Civil Procedure Code specified under Article 82 (4) of this Proclamation.

ሮ፸፰. በማይንቀሳቀስ ንብረት ተጓዳኝ ላይ መብትን ስለማስከበር

፩/ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ በማይንቀሳቀስ ንብረት ተጓዳኝ ላይ ያገኘውን የዋስትና መብት በዚህ ክፍል ድንጋጌዎች መሠረት ማስከበር ይችላል።

፪/ የአንድ ግዴታ አፈጻጸም በመያዣ ሰጪው ተንቀሳቃሽም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት ዋስትና ከተገባለት ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ በምርጫው፦

ሀ) በተንቀሳቃሽ ንብረት የዋስትና መብት ማስከበር ድንጋጌዎች መሠረት በተንቀሳቃሽ ንብረቱ ላይ ያለውን የዋስትና መብት፣

ለ) በማይንቀሳቀስ ንብረት ዋስትና መብት የማስከበር ድንጋጌዎች መሠረት በማይንቀሳቀስ ንብረቱ ላይ ያለውን የዋስትና መብት፣ ወይም

ሐ) በማይንቀሳቀስ ንብረት ዋስትና መብት የማስከበር ድንጋጌዎች መሠረት በሁለቱም ዓይነት ንብረቶች ላይ ያገኘውን የዋስትና መብት፣

ማስከበር ይችላል።

ሮ፸፱. መልሶ ስለመውሰድ መብት

፩/ በዚህ ክፍል ድንጋጌዎች የመብት ማስከበር ሂደት መብቱ የተነካበት ማንኛውም ሰው ተገቢ የሆነ የማስከበር ወጪን ጨምሮ ዋስትና የተገባለት ግዴታን በመክፈል ወይም በመፈጸም መያዣውን መልሶ መውሰድ ይችላል።

፪/ መያዣ ሰጪው ያለው መያዣውን መልሶ የመውሰድ መብት ሌላ ማንኛውም ሰው መያዣውን ለመውሰድ ካለው መብት ቀዳሚነት ይኖረዋል።

78. Enforcement Against Accessories to Immovable

1/ The secured creditor may enforce a security right in an accessory to immovable in accordance with this Part.

2/ If an obligation is secured by both a movable property and immovable property of a grantor, the secured creditor may elect to enforce:

a) the security right in the movable property under the provisions on enforcement of a security right in movable property;

b) the encumbrance on the immovable property under the law governing enforcement of encumbrances on immovable property; or

c) both rights under the law governing enforcement of encumbrances on immovable property.

79. Right of Redemption

1/ Any person whose right is affected by the enforcement process in accordance with the provisions of this Part is entitled to redeem the collateral by paying or otherwise performing the secured obligation in full, including the reasonable cost of enforcement.

2/ The grantor's right to redeem the collateral shall have priority over any other person's right to redeem the collateral.

ሸ/ መያዣውን መልሶ የመውሰድ መብትን መያዣው እስከሚሸጥ፣ ወይም እስከሚተላለፍ ወይም ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ እስከሚወስደው ወይም ለዚሁ ዓላማ ውሉ እስከሚፈጸም ድረስ መጠቀም ይቻላል።

፹. ቀዳሚ ደረጃ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መብቱን ለማስከበር ስለሚኖረው የመሬነት መብት

፩/ ሌላ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ወይም በህግ ወይም በፍርድ የገንዘብ ጠያቂነት መብት የተሰጠው ሰው የዋስትና መብቱን ማስከበር ቢጀምርም ከነዚህ መብቶች የቀዳሚነት መብት ያለው ገንዘብ ጠያቂ ዋስትናው ከመሸጡ፣ ከመተላለፉ ወይም በሌላኛው ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ከመወሰዱ ወይም ይኸው ገንዘብ ጠያቂ ለዚሁ ዓላማ ውሉን ከመፈጸሙ በፊት በማንኛውም ጊዜ የዋስትና መብት የማስከበር ሂደትን በበላይነት መምራት መጀመር ይችላል።

፪/ ቀዳሚ ደረጃ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መብት የማስከበር ሂደትን በበላይነት የመምራት መብት እንድ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ በዚህ አዋጅ በተደነገገ ማንኛውም መንገድ መብቱን ለማስከበር እንዲችል የተሰጠውን መብት ያካትታል።

፹፩. ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መያዣውን በይዞታው ሥር ለማድረግ ስላለው መብት

፩/ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ፦

ሀ) ያለፍርድ ቤት ማመልከቻ መያዣውን በይዞታው ሥር ማድረግ እንደሚችል መያዣ ሰጪው በዋስትና ስምምነቱ ከፈቀደ፥

ለ) መያዣውን በይዞታው ሥር ለማድረግ በሚሞክርበት ጊዜ መያዣ ሰጪው ወይም መያዣውን በይዞታው ሥር ያደረገ ማንኛውም ሌላ ሰው ካልተቃወመ፥

መያዣውን በይዞታው ሥር ማድረግ ይችላል።

3/ The right of redemption may be exercised until the collateral is sold or otherwise disposed of acquired or collected by the secured creditor or until the conclusion of an agreement by the secured creditor for that purpose.

80. Right of the Higher-Ranking Secured Creditor to Take Over Enforcement

1/ Despite commencement of enforcement by another secured creditor or a non-consensual creditor, a secured creditor whose security right has priority over that of the enforcing creditor is entitled to take over the enforcement process at any time before the collateral is sold or otherwise disposed of, or acquired by the secured creditor or until the conclusion of an agreement by the secured creditor for that purpose.

2/ The right of the higher-ranking secured creditor to take over the enforcement process includes the right to enforce by any method available to a secured creditor under this Proclamation.

81. Right of the Secured Creditor to Possess the Collateral

1/ The secured creditor is entitled to obtain possession of the collateral if:

a) the grantor has consented in the security agreement to the secured creditor obtaining possession without applying to a court; and

b) at the time the secured creditor attempts to obtain possession of the collateral, the grantor or any other person in possession of the collateral does not object.

ሸ/ መያዣ ሰጪው ወይም መያዣውን በይዞታው ሥር ያደረገ ማንኛውም ሌላ ሰው መያዣውን ዋስትና ላለው ገንዘብ ጠያቂ ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆነ የመያዣ ምዝገባ ጽሕፈት ቤት የፖሊስ ኃይል ርክክቡን እንዲያስፈጽም የማዘዝ ሥልጣንና ኃላፊነት አለው።

ቀ/ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መያዣውን ሳያወሰድ በመያዣ ሰጪው ቅጥር ግቢ ውስጥ እንዳለ አገልግሎት መስጠት እንዳይችል ለማድረግ ወይም ለማስተላለፍ ይችላል።

፹፪. ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መያዣውን ለማስተላለፍ ስላለው መብት

ሀ/ ግዴታ አለመፈጸምን ተከትሎ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መያዣውን ባለበት ሁኔታ ወይም ከንግድ አሠራር አንፃር ተገቢ የሆነ ዝግጅት ወይም ማሻሻያ በማድረግ ለመሸጥ፣ ለማስተላለፍ፣ ለማከራየት ወይም ለመጠቀም የሚያስችል ፈቃድ ለመስጠት ይችላል።

ለ/ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መያዣው የሚሸጥበት፣ የሚተላለፍበት፣ የሚከራይበት ወይም ለመጠቀም የሚያስችል ፈቃድ የሚሰጥበትን መንገድ፣ ሁኔታ፣ ጊዜ፣ ቦታና ሌሎች ሁኔታዎች ማመቻቸት ይችላል። ይህም መያዣውን በተናጠል፣ በክፊል ወይም በጠቅላላ የመሸጥ፣ የማስተላለፍ፣ የማከራየት ወይም ለመጠቀም የሚያስችል ፈቃድ የመስጠት ምርጫን ይጨምራል።

ሐ/ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ የመያዣውን ባለቤትነት በሐራጅ ለገዛው ሰው ማስተላለፍ፣ ወይም በሁለተኛው ሐራጅ ገዢ ካልቀረበ በመጀመሪያው ሐራጅ በተወሰነው የመነሻ ዋጋ መያዣውን የመውሰድና ባለቤትነቱም እንዲተላለፍለት ማድረግ ይችላል።

2/ If the grantor or any other person in possession of the collateral objects to give possession to the secured creditor the Collateral Registry Office shall have the power and duty to order the police force to execute possession.

3/ The secured creditor may, without removal, render the collateral unusable and dispose of it on the grantor's premises.

82. Right of the Secured Creditor to Dispose of the Collateral

1/ After default, the secured creditor is entitled to sell or otherwise dispose of lease or license the collateral in its present condition or following any commercially reasonable preparation or processing.

2/ The secured creditor may select the method, manner, time, place and other aspects of the sale or other disposition lease or license, including whether to sell or otherwise dispose of, lease or license collaterals individually, in groups or as a whole.

3/ The secured creditor may transfer the ownership of the collateral to the buyer at a public auction or if no buyer appears at the second auction, to acquire the property at the floor price set for the first auction and have the ownership of the property transferred to it.

፬/ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ሐራጅን ከመረጠ የጨረታ ሂደቱ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ከቁጥር ፫፻፶፬-፬፻፵፱ በተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደአግባብነታቸው መሠረት መፈጸም አለበት፡፡

፭/ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት የሚፈፀም መያዣን ማስተላለፍ መያዣ ሰጪውን በመወከል እንደተፈፀመ ይቆጠራል፡፡

፹፫. መያዣን ለማስተላለፍ የሚሰጥ ማስታወቂያ

፩/ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መያዣውን የማስተላለፍ ፍላጎት ካለው የአሥር የሥራ ቀናት ማስታወቂያ፡-

ሀ) ለመያዣ ሰጪው እና ለባለዕዳው፤

ለ) በመያዣው ላይ መብት እንዳለው በጽሑፍ ላሳወቀው ማንኛውም ሰው፤

ሐ) የዋስትና መብት ማስታወቂያ ላስመዘገበ ማንኛውም ዋስትና ያለው ሌላ ገንዘብ ጠያቂ፤ እና

መ) ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መያዣውን በይዞታው ሥር በሚያደርግበት ጊዜ መያዣው ቀደም ሲል በይዞታው ሥር ለነበረ ማንኛውም ዋስትና ያለው ሌላ ገንዘብ ጠያቂ፣

መስጠት አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚሰጥ ማስታወቂያ፡-

ሀ) መያዣ ሰጪውን እና ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂን፣

ለ) የመያዣውን መግለጫ፣

ሐ) ወለድና ተገቢ የሆነ የማስከበሪያ ወጪ ግምትን ጨምሮ ዋስትናው የተጠበቀ ግዴታን ለመፈጸም የሚያስፈልገውን የገንዘብ መጠን፣

መ) የታቀደው ማስተላለፍ ስለሚፈጸምበት ሁኔታ፣

4/ If the creditor opts to use public auction, the auction procedure shall mutatis mutandis, follow the provisions of Article 394-449 of the Civil Procedure Code.

5/ The disposition made in accordance with this proclamation shall be deemed to have been executed on behalf of the grantor.

83. Notification of Disposition of the Collateral

1/ The secured creditor shall give a ten working days notification of its intention to dispose of the collateral to:

a) the grantor and the debtor;

b) any person with right in the collateral that notifies in writing the secured creditor of those right;

c) any other secured creditor that registered a security right notification with respect to the collateral; and

d) any other secured creditor that was in possession of the collateral at the time when the enforcing secured creditor took its possession.

2/ In accordance with Sub-article (1) of this Article, the notice shall:

a) identify the grantor and the secured creditor;

b) contain a description of the collateral;

c) state the amount required to satisfy the secured obligation including interest and a reasonable estimate of the cost of enforcement;

d) identify the manner of the intended disposition; and

ሠ) ከመቼ ቀን በኋላ መያዣው እንደሚሸጥ፣ እንደሚተላለፍ፣ እንደሚከራይ ወይም ለመጠቀም የሚያስችል ፈቃድ እንደሚሰጥ ወይም በሐራጅ የሚሸጥበትን ጊዜና ቦታ፣ መግለፅና ማመልከት አለበት፡፡

e) state the date after which the collateral will be sold or otherwise disposed of, leased or licensed, or provide the time and place of a public disposition.

፫/ ማስታወቂያው ይዘቱን በተገቢው ሁኔታ ይገልጻል ተብሎ በሚጠበቅ ቋንቋ መሆን አለበት፡፡ ሆኖም ለመያዣ ሰጪው የሚሰጠው ማስታወቂያ የዋስትና ስምምነቱ በተጻፈበት ቋንቋ ከሆነ በቂ ነው፡፡

3/ The notice shall be in a language that is reasonably expected to inform its recipients about its contents. However, it is sufficient if the notice to the grantor is in the language of the security agreement.

፬/ የማስታወቂያው ይዘት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከተውን መረጃ ካካተተ በንዑስ አንቀጹ ከተመለከተው ውጭ የሆነ መረጃ ቢያገኝም ወይም ከባድ ስህተት የማያስከትሉ አነስተኛ ግድፈቶች ቢኖሩትም በቂ ይሆናል፡፡

4/ The contents of a notice providing substantially the information specified in Sub Article (2) of this Article is sufficient, even if the notice includes information not specified in that Sub Article or minor errors that are not seriously misleading.

፭/ ማስታወቂያ መስጠት የማያስፈልገው መያዣው፡-

5/ The notice need not be given if the collateral:

ሀ) ዋስትና ባለው ገንዘብ ጠያቂ ይዞታ ሥር ከሆነ በኋላ ያሉት አሥር የሥራ ቀናት ከማለቃቸው በፊት የሚበላሽ ከሆነ፣

a) may perish before the end of ten working days after the secured creditor obtained possession of such collateral;

ለ) ዋጋው በፍጥነት የሚወርድ ከሆነ፣

b) may decline in value speedily;

ሐ) በታወቀ ገበያ ላይ የሚሸጥ ዓይነት ከሆነ፣ ወይም

c) is of a kind sold on a recognized market; or

መ) ለእንክብካቤውና ለጥበቃው የሚያስፈልገው ወጪ ከዋጋው አንፃር እጅጉን የሚበልጥ ከሆነ፣

d) the cost of care and storage of the collateral is disproportionately large relative to its value.

ነው፡፡

፹፬. ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ከመያዣው ሙተላለፍ የሚገኝ ተያያዥ ገቢን ለማከፋፈል ስላለው መብት

84. Right of the Secured Creditor to Distribute the Proceeds of a Disposition of a Collateral

፩/ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፹፪ መሠረት በሚደረግ የመያዣ ማስተላለፍ ሂደት የሚገኝ ተያያዥ ገቢን፡-

1/ The secured creditor shall apply the proceeds of disposition under Article 82 in the following order to:

ሀ) መያዣውን መልሶ ለመውሰድ፣ ለመያዝ፣ ለማስተላለፍ ዝግጁ ለማድረግ፣ ለማሻሻል እና ለማስተላለፍ ለሚወጣ ተገቢ ወጪ፣

ለ) መያዣውን ለማስተላለፉ መነሻ በሆነው የዋስትና መብት ላይ ያሉ ግዴታዎችን ለመወጣት፣ እና

ሐ) የገቢው ክፍፍል ከመጠናቀቁ በፊት የበታች የሆነ የዋስትና መብት ወይም ሌላ ዋስትና ያለው ሰው ድርሻው እንዲሰጠውና ዋስትና የተገባላቸው ግዴታዎች እንዲፈጸሙ ጥያቄ ካቀረበ፣

በዚህ ንዑስ አንቀጽ ቅደም ተከተል መሠረት ክፍያውን ይፈጽማል፡፡

፪/ የበታች የሆነ የዋስትና መብት ወይም ሌላ ዋስትና ያለው ሰው ስለጥቅሙ ወይም ስለዋስትና መብቱ ሌላ ዋስትና ባለው ገንዘብ ጠያቂ ከተጠየቀ ተገቢውን ማረጋገጫ ተገቢ በሆነ ጊዜ ውስጥ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ ይህ ካልተፈፀመ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ሐ) መሠረት የበታች የሆነ የዋስትና ባለመብቱ የሚያቀርብለትን ጥያቄ ለማክበር አይገደድም፡፡

፫/ በተወዳዳሪ ባለመብቶች መካከል የመብት ወይም የቀዳሚነት ክርክር ሲነሳ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ የፍርድ ቤት ወይም ሌላ ሥልጣን ያለው አካል ትዕዛዝን የያዘ ባለመብት እስኪመጣ ድረስ ተራፊውን ገንዘብ ወለድ በሚያስገኝ ዝግ ሂሳብ ውስጥ እስከ ስልሳ ቀናት ለማስቀመጥና ሂሳቡንም ይዞ ለማቆየት ይችላል፡፡

፬/ የዋስትና መብት በማስከበር የሚገኘው ገቢ ዋስትናው የተጠበቀ ግዴታን ለመወጣት ከዋለ በኋላ ላልተከፈለው ቀሪ ዕዳ ባለዕዳው ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

a) the reasonable expense of retaking, holding, preparing for disposition, processing and disposing of the collateral;

b) the satisfaction of obligations secured by the security right under which the disposition is made; and

c) the satisfaction of obligations secured by any subordinate security right or other subordinate lien in the collateral if the secured creditor receives from the holder of the subordinate security right or other lien a demand for proceeds before distribution of the proceed is completed.

2/ If requested by the secured creditor, a holder of a subordinate security right or other lien shall furnish reasonable proof of the interest or lien within a reasonable time. Unless the holder does so, the secured creditor need not comply with the holder's demand under Sub Article (1) (c) of this Article.

3/ Where there is a dispute as to the entitlement or priority of any competing claimant, the enforcing secured creditor may deposit the surplus in an interest bearing blocked account within sixty days and keep the account until a claimant comes up with an order of court or any competing organ.

4/ A debtor remains liable for any shortfall owing after application of the proceeds of enforcement to the secured obligation.

፫/ መያዣ ሰጪው ለተረፈው ገቢ ባለመብት ይሆናል።

፹፭. ዋስትና ለተገባለት ግዴታ ሙሉ ወይም ከፊል የአፈጻጸም መያዣውን ስለመውሰድ

፩/ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ዋስትና ለተገባለት ግዴታ ሙሉ ወይም ከፊል አፈጻጸም ሲባል አንድ ወይም ከአንድ በላይ የዋስትና መያዣዎችን ለመውሰድ የጽሑፍ ምክረ ሐሳብ መያዣዎቹ ከመተላለፋቸው በፊት ወይም በሚተላለፉበት ጊዜ ሊያቀርብ ይችላል።

፪/ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ምክረ ሐሳቡን:-

ሀ) ለመያዣ ሰጪው፡

ለ) ዋስትና የተገባለት ግዴታ ከፊል አፈጻጸምን በሚመለከት ብቻ ከሆነ ለባለዕዳው፡

ሐ) ለመያዣ ሰጪው ከመላኩ ወይም መያዣ ሰጪው ምክረ ሐሳቡን ከመቀበሉ አሥር ቀናት አስቀድሞ በመያዣው ላይ ሰላለው መብት በጽሑፍ ሳሳወቀው ማንኛውም ሰው፡

መ) ለመያዣ ሰጪው ከመላኩ ወይም መያዣ ሰጪው ምክረ ሐሳቡን የመቀበል መብቱን ከመተው ከአሥር ቀናት አስቀድሞ መያዣውን አስመልክቶ ማስታወቂያ ላስመዘገበ ሌላ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ፣ እና

ሠ) መያዣውን በይዞታው ሥር ባደረገ ጊዜ መያዣው ቀደም ሲል በይዞታው ሥር ለነበረ ሌላ ማንኛውም ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ፡

መላክ ይኖርበታል።

5/ The grantor shall be entitled to any surplus.

85. Acquisition of Collateral in Total or Partial Satisfaction of the Secured Obligation

1/ The secured creditor may propose in writing, before or during disposition to acquire one or more of the assets subject to a security right in total or partial satisfaction of the secured obligation.

2/ The secured creditor shall send the proposal to:

a) the grantor;

b) the debtor but only in the case of a proposal to accept the collateral in partial satisfaction of the secured obligation;

c) any person with rights in the collateral that has notified in writing the secured creditor of those right at least ten working days before the notice is sent to the grantor or the grantor waived the right to receive the proposal;

d) any other secured creditor that registered a notice with respect to the collateral at least ten working days before the notice is sent to the grantor or the grantor waived the right to receive the proposal; and

e) any other secured creditor that was in possession of the collateral at the time the secured creditor took possession.

ሸ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የቀረበ ምክረ ሐሳብ:-

ሀ) ዋስትና ያለው ግንዘብ ጠያቂንና የመያዣ ሰጪውን ማንነት፣

ለ)ማስታወቂያው ቡተላከበት ቀን ያልተከፈለውን ዕዳ ከነወለዱና ዋስትና ያለው ግንዘብ ጠያቂ መብቱን ለማስከበር ያወጣውን ወጪ እንዲሁም መያዣውን በመውሰድ ግዴታውን ለመወጣት የሚያስፈልገውን መጠን፣

ሐ) ዋስትና ያለው ግንዘብ ጠያቂ ለግዴታው አፈጻጸም መያዣውን የሚወስደው በሙሉ ወይም በከፊል መሆኑን፣

መ) መያዣውን፣

ሠ) ባለዕዳው ወይም መያዣ ሰጪው በአንቀጽ ፹፱ መሠረት መያዣውን መልሶ ለመውሰድ ያለውን መብት፣ እና

ረ) ዋስትና ያለው ግንዘብ ጠያቂ መያዣውን ከመቼ ቀን በኋላ እንደሚወሰድ፣

ለይቶና በዝርዝር መግለፅ አለበት።

፬/ ዋስትና ያለው ግንዘብ ጠያቂ መያዣውን የሚወስደው:-

ሀ) ዋስትናው ለተጠበቀ ግዴታ ሙሉ አፈጻጸም ከሆነ ማስታወቂያውን የመቀበል መብት ካለው ማንኛውም ሰው ማስታወቂያው በተላከለት አሥራ አምስት የሥራ ቀናት ውስጥ የጽሑፍ ተቃውሞ ካልቀረበለት፣ እና

ለ) ዋስትናው ለተጠበቀ ግዴታ ከፊል አፈጻጸም ከሆነ እያንዳንዱ ማስታወቂያው የተላከለት ሰው ማስታወቂያው በተላከ በአሥራ አምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ፈቃደኛነቱን በጽሑፍ ካረጋገጠ ብቻ፣

ነው።

3/ In accordance with Sub-article (1) of this Article, the proposal shall:

a) identify the secured creditor and grantor;

b) specify the amount owed as of the date the notification is sent, including interest and the cost of enforcement, and the amount of the obligation that is proposed to be satisfied by acquiring the collateral;

c) indicate whether the secured creditor intends to acquire the collateral in total or partial satisfaction of the secured obligation;

d) describe the collateral;

e) refer to the right of the debtor or the grantor to redeem the collateral as provided in Article 79; and

f) state the date after which the collateral will be acquired by the secured creditor.

4/ The secured creditor acquires the collateral:

a) in the case of a proposal for the acquisition of the collateral in full satisfaction of the secured obligation, unless the secured creditor receives an objection in writing from any person entitled to receive such a notice within fifteen working days after the notice is sent to that person; and

b) in the case of a proposal for the acquisition of the collateral in partial satisfaction of the secured obligation, only if the secured creditor receives the affirmative consent of each addressee of the notice in writing within fifteen working days after the notice is sent to that person.

፹፮. በመያዣው ላይ ስለሚገኝ መብት

፩/ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መያዣውን ከሸጠ ወይም ካስተላለፈ፣ ገዢው ወይም የተላለፈለት ሰው ከሚያፈቱ ወይም ከአስተላላፊው ሌላ ቀዳሚ የዋስትና መብት ያለው ገንዘብ ጠያቂ ከሌለ በስተቀር መያዣውን የማስያዝ መብት የሚያገኘው መያዣውን ከሸጠውና የበታች የሆነ ተወዳዳሪ የዋስትና መብት ነጻ በሆነ መንገድ ነው።

፪/ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መያዣውን ከከራየ ወይም የመጠቀም ፈቃድ ከሰጠ፣ ተከራዩ ወይም ፈቃዱ የተሰጠው ሌላ ቀዳሚ የዋስትና መብት ያለው ገንዘብ ጠያቂ ከሌለ በስተቀር ኪራዩ ወይም ፈቃዱ በሥራ ላይ ባለ ጊዜ የሚያስገኘውን ጥቅም ያገኛል።

፫/ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ከዚህ ክፍል ድንጋጌዎች ውጭ መያዣውን ከሸጠ ወይም ካስተላለፈ፣ ከከራየ ወይም የመጠቀም ፈቃድ ከሰጠ ገዢው ወይም የተላለፈለት ሰው፣ ተከራዩ ወይም ባለፈቃዱ በመያዣው ላይ መብት ወይም ተጠቃሚነትን የሚያገኘው ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ የዚህን ክፍል ድንጋጌዎች በመጣስ መያዣ ሰጪውን ወይም የሌላን ሰው መብት ጉልህ በሆነ አኳኋን መጉዳቱን ካላወቀ ነው።

፹፯. ከተሰብሳቢ ሂሳብ፣ ከተላላፊ የገንዘብ ሰነድ፣ በተቀማጭ ሂሳብ ገቢ ከተደረገ ገንዘብ ወይም ከሴኩሪቲ ክፍያ ስለመሰብሰብ እና ስለመጠየቅ መብት

፩/ ከግዴታ አለመወጣት በኋላ በተሰብሳቢ ሂሳብ፣ በተላላፊ የገንዘብ ሰነድ ወይም ሴኩሪቲ ላይ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ከተሰብሳቢው ሂሳብ ባለዕዳ፣ ከተላላፊ የገንዘብ ሰነዱ ተገዳጅ ወይም ከሴኩሪቲ አውጪው ክፍያ መሰብሰብ ይችላል።

86. Rights Acquired in Collateral

1/ If a secured creditor sells or otherwise disposes of the collateral, a buyer or other transferee acquires the grantor's right in the asset free of the rights of the enforcing secured creditor and any subordinate competing claimant, except the right that have priority over the security right of the enforcing secured creditor.

2/ If a secured creditor leases or licenses the collateral, a lessee or licensee is entitled to the benefit of the lease or license during its term, except as against creditors with right that have priority over the right of the enforcing secured creditor.

3/ If a secured creditor sells or otherwise disposes of leases or licenses the collateral not in accordance with the provisions of this Part, a buyer or other transferee, lessee, or licensee of the collateral acquires the right or benefit, provided that it had no knowledge of a violation of the provisions of this Part that materially prejudiced the right of the grantor or another person.

87. Collection of Payment Under a Receivable, Negotiable Instrument, Right to Payment of Funds Credited to a Deposit Account or Security

1/ After default, a secured creditor with a security right in a receivable, negotiable instrument, or security is entitled to collect payment from the debtor of the receivable, obligor under the negotiable instrument, or issuer of the security.

፪/ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ክግዴታው አለመወጣት አስቀድሞ የመያዣ ሰጪውን ፈቃድ ካገኘ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ክፍያ የመሰብሰብ መብቱን መጠቀም ይችላል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) መሠረት ክፍያ የመሰብሰብ መብቱን የሚያስፈጽም ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ የክፍያ መያዣውን በሚደግፍ ወይም በሚያረጋግጥ ማንኛውም ግላዊ ወይም የንብረት መብት ላይም መብቱን ማስከበር ይችላል።

፬/ በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፩)-(፫) ባለው መሠረት ክፍያ የመሰብሰብ መብቱን ከአንቀጽ ፸ እስከ ፸፬ በተደነገገው መሠረት ተፈጻሚ ያደርጋል።

፭/ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ያለውን መብት በአንቀጽ ፲፯ (፪) መሠረት በቁጥጥር ስምምነት ተፈጻሚ ካደረገ ብቻ ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ተቀማጭ ገንዘብ የመቀበል መብት ካላቸው የፋይናንስ ተቋማት ክፍያ መሰብሰብ ይችላል።

፹፰. የተሰብሳቢ ሂሳብ መብት ሙሉ በሙሉ የተላለፈለት ሰው ስለሚሰበስበው ክፍያ

የተሰብሳቢ ሂሳብ መብት ሙሉ በሙሉ የተላለፈለት ሰው ክፍያውን አስተላላፊው ግዴታውን ከመወጣቱ በፊት ወይም በኋላ መሰብሰብ ይችላል።

ክፍል ስምንት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፹፱. ከቴምብር ቀረጥ ነፃ መሆን

በዚህ አዋጅ መሠረት የዋስትና መብትን ለመመሥረት የሚደረግ ስምምነት ወይም ግብይት ከቴምብር ቀረጥ ክፍያ ነፃ ነው።

2/ The secured creditor may exercise the right to collect under Sub Article (1) of this Article even before default with the consent of the grantor.

3/ A secured creditor exercising the right to collect under Sub Article (1) or (2) of this Article is also entitled to enforce any personal or property right that secures or supports payment of the collateral.

4/ The right of the secured creditor to collect payment from the debtor of the receivable under Sub Articles (1)-(3) of this Article is subject to Articles 70-74.

5/ The secured creditor may collect payment from the financial institutions authorized to receive deposits without a court order only if it has made its security right effective against third parties by a control agreement pursuant to Article 17 (2).

88. Collection of Payment Under a Receivable by an Outright Assignee

In the case of an outright assignment of a receivable, the assignee is entitled to collect the receivable before or after default of the assignor.

PART EIGHT

MISCELLANEOUS PROVISIONS

89. Exemption from Stamp Duty

Transactions that create security right governed by this Proclamation is exempted from payment of stamp duty.

፯. ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት በተጀመሩ ክርክሮች ላይ ተፈፃሚ አለመሆኑ

፩/ ይህ አዋጅ ከመፅናቱ በፊት የተጀመረ የፍርድ ቤት ወይም የሽምግልና ጉባዔ ክርክር ላይ የቀደምት ሕግ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

፪/ ይህ አዋጅ ከመፅናቱ በፊት የተጀመረ ቀደምት የዋስትና መብት አፈጻጸም በቀደምት ሕግ መሠረት ሊቀጥል ይችላል፡፡

፺፩. መብትና ግዴታዎችን ስለማስተላለፍ

፩/ በሌሎች ሥራ ላይ ባሉ ሕጐችና ድንጋጌዎች መሠረት:-

ሀ) የትራንስፖርት ሚኒስቴር በተሽከርካሪዎች፡

ለ) የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በኮንስትራክሽን መሣሪያዎች፡ እና

ሐ) የንግድ ሚኒስቴር በንግድ ተቋማትና በዱቤ ግዥ ውል፡

በተንቀሳቃሽ ንብረት፣ የዋስትና መብት ምዝገባ ጋር በተገናኘ ያሏቸው መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት ለመያዣ ምዝገባ ጽሕፈት ቤት ተላልፈዋል፡፡

፪/ ማንኛውም ሌላ መንግሥታዊ ተቋም በሌሎች ሥራ ላይ ባሉ ሕጐች ድንጋጌዎች መሠረት የሌሎች ግዑዝ እና ግዑዝነት የሌላቸው ተንቀሳቃሽ ወጪቶች የዋስትና መብት ምዝገባ ጉዳዮች ጋር በተገናኘ ያለው መብትና ግዴታ በዚህ አዋጅ ለመያዣ ምዝገባ ጽሕፈት ቤት ተላልፏል፡፡

90. Inapplicability of This Proclamation to Actions Commenced before its Entry into Force

1/ prior law applies to a matter that is the subject of proceedings before a court or arbitral tribunal commenced before the entry into force of this Proclamation.

2/ if enforcement of a prior security right commenced before the entry into force of this Proclamation, the enforcement may continue under the prior law.

91. Transfer of Right and Obligations

1/ By the provisions of other laws, currently in force, the rights and obligations of the:

a) Ministry of Transport with respect to matters relating to registration of security rights on vehicles;

b) Ministry of Construction with respect to matters relating to registration of security rights on Construction Machineries and Equipments; and

c) Ministry of Trade with respect to matters relating to registration of security rights on Business Mortgage and Hire Purchase;

with respect to registration of moveable collaterals are hereby transferred to the Collateral Registry Office.

2/ The right and obligation of any other government institution by the provisions of other laws currently in force, with respect to matters relating to registration of security rights on other corporal and incorporeal assets are hereby transferred to the Collateral Registry Office.

ሸ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ግዑዝ እና ግዑዛነት ለሌለው ሀብት የባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የመስጠት ኃላፊነት የተጣለባቸው ተቋማት ባለቤትነቱን ከማስተላለፋቸው በፊት መብቱ ከዋስትና ነፃ መሆኑን ከዋስትና መዝገብ ማጣራትና ማረጋገጥ አለባቸው።

3/ Without prejudice to Sub Article (1) and (2) of this Article, institutions responsible for providing title deeds for corporal and incorporeal assets shall check with the Collateral Registry and ascertain whether or not the asset has been free from any pledged before effecting title transfer.

፺፪. ቀደምት የዋስትና መብት በሦስተኛ ወገን ላይ ስላለው ተፈፃሚነት

92. Third-Party Effectiveness of a Prior Security Right

፩/ በቀደምት ሕግ መሠረት በሦስተኛ ወገን ላይ ተፈፃሚ የነበረ የዋስትና መብት ከዚህ በታች ከተገለጹት አንደኛው በቅድሚያ እስከሚከሰት ድረስ በሦስተኛ ወገን ላይ ተፈፃሚ ሆኖ ይቀጥላል፦

1/ A prior security right that was effective against third parties under prior law continues to be effective against third parties under this Proclamation ~~until the~~ earlier of:

ሀ) በቀደምት ሕግ መሠረት በሦስተኛ ወገን ላይ ያለው ተፈፃሚነት ይህ አዋጅ ተግባራዊ ከሆነ በኋላ ባሉት አሥራ ሁለት ወራት ጊዜ ማብቃት፡ ወይም

a) the time it would have ceased to be effective against third parties under prior law within twelve months from entry into force of this Proclamation; or

ለ) ይህ አዋጅ ከፀና በኋላ ባሉት አሥራ ሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ የዋስትና መብቱን በመያዣ መዝገቡ የተመዘገበ እንደሆነ ነው።

b) registration of security right in the registry within twelve months after the entry into force of this Proclamation.

፪/ ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት በመያዣ ሰጪው እና ዋስትና ባለው ገንዘብ ጠያቂ መካከል ቀደምት የዋስትና መብት ለመመስረት በጽሑፍ የተደረገ ስምምነት መያዣ ሰጪው ይህ አዋጅ ከፀና በኋላ ማስታወቂያው እንዲመዘገብ ፈቃደኛነት ያለው መሆኑን ለማሳወቅ በቂ ነው።

2/ A written agreement between the grantor and the secured creditor creating or providing for a prior security right entered into before the entry into force of this Proclamation is sufficient to constitute authorization by the grantor for the registration of a notice after the entry into force of this Proclamation.

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ቀደምት የዋስትና መብት በሦስተኛ ወገን ላይ ያለው ተፈፃሚነት ከማብቃቱ በፊት የዚህ አዋጅ በሦስተኛ ወገን ላይ ያለው ተፈፃሚነት ቅድመ ሁኔታዎች ከተሟሉ በዚህ አዋጅ መሠረት ቀደምት የዋስትና መብቱ በቀደምት ሕግ መሠረት በሦስተኛ ወገን ላይ ተፈፃሚ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ ተፈፃሚ ሆኖ ይቀጥላል።

3/ If the third-party effectiveness requirements of this Proclamation are satisfied before the third-party effectiveness of a prior security right ceases in accordance with Sub Article (1) of this Article, the security right continues to be effective against third parties under this Proclamation from the time when it was made effective against third parties under prior law.

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ቀደምት የዋስትና መብት በሦስተኛ ወገን ላይ ያለው ተፈፃሚነት ከግብቃቱ በፊት የዚህ አዋጅ የሦስተኛ ወገን ተፈፃሚነት ቅድመ ሁኔታዎች ካልተሟሉ ቀደምት የዋስትና መብቱ በሦስተኛ ወገን ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው በዚህ አዋጅ መሠረት በሦስተኛ ወገን ላይ ተፈፃሚ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ ነው።

4/ If the third-party effectiveness requirements of this Proclamation are not satisfied before the third-party effectiveness of a prior security right ceases in accordance with Sub Article (1) of this Article, the prior security right is effective against third parties only from the time it is made effective against third parties under this Proclamation.

፺፫. የተሻሩና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

93. Repealed and Inapplicable Laws

፩/ በባንክ መያዣ ስለተያዘ ንብረት በወጣው አዋጅ ቁጥር ፺፯/፲፱፺፯ ሙሉ በሙንቀሳቃሽ ንብረት የመያዣ መብት ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ ድንጋጌዎች በሙሉ በዚህ አዋጅ ተሽረዋል።

1/Provisions related to movable property security rights stipulated under Property Mortgaged or Pledged with Banks Proclamation No.97/1998 are hereby repealed.

፪/ ስለንግድ ተቋም የዋስትና መያዣ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፺፰/፲፱፺፯ በዚህ አዋጅ ተሽሯል።

2/Business Mortgage Proclamations No. 98/1998 is hereby repealed.

፫/ ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ህግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈፃሚነት አይኖረውም።

3/No law, regulation, directive or practice shall, in so far as it is inconsistent with this Proclamation may be applicable with respect to matters covered under this Proclamation.

፺፬. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

94. Power to Issue Regulation and Directive

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልግ ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

1/ The Council of Ministers may issue regulation for, or with respect to, any matter under this Proclamation that is necessary for carrying out or giving effect to this Proclamation.

፪/ የመያዣ ምዝገባ ጽሕፈት ቤት ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

2/ The Collateral Registry Office may issue directives necessary for the implementation of this Proclamation and Regulations in accordance with Sub Article (1) of this Article.

፺፭. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ራሱን የቻለ የመያዣ ምዝገባ ጽሕፈት ቤት በደንብ እስኪቋቋም ድረስ፣ የመያዣ ምዝገባ ጽሕፈት ቤትን ለማደራጀት፣ የመያዣ መዝገብ ሥርዓትን ለመዘርጋት፣ ሥራ ለማስጀመር፣ እና ሬጅስትራሩን ለመሾም፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ስልጣን ተሰጥቶታል።

95. Transitory Provision

Until such time of the establishment of an autonomous Collateral Registry Office by regulation, the National Bank of Ethiopia is hereby empowered to establish the Collateral Registry Office, the Collateral Registry, operationalize the Collateral Registry and appoint the Registrar.

፺፮. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን የ፲፪ ወራት ማለቅ ወይም የመያዣ መዝገቡ ሥራ መጀመር ከሁለቱ በቀደመው በአንደኛው ቀን የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ነሐሴ ፩ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

ሣህለወርቅ ዘውዴ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ

ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

96. Effective Date

This Proclamation shall come into force on the date of the expiry of 12 months after publication in the Negarit Gazette or the commencement of operation of the Collateral Registry, whichever comes first.

Done at Addis Ababa, this 7th day of August, 2019

SAHLEWORK ZEWDIE

PRESIDENT OF THE FEDERALDEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA